የደስታ መንገድ

ለተሻለ ሕይወት የሚረዳ መሠረታዊ መመሪያ



ለ: _____

ከ: _____

ይህንን መጽሐፍ መጠቀም የሚቻልበት መንገድ

የምታውቃቸውን ሰዎችና ጓደኞችህን መርዳት እንደምትፈልግ የታወቀ ነው።

የሩቅ ሰውም ቢሆን ባሕርይው በአንተ ሕልውና ላይ ተጽዕኖ የሚኖረውን አንድ ሰው ምረጥ።

በፊተኛው ሽፋን ላይ በሚገኘው የላይኛው መስመር ላይ ስሙን ጻፍ።

በሽፋኑ ገጽ ላይ በሚገኘው ሁለተኛ መስመር ላይ የራስህን ስም ጻፍ።

ይህንን መጽሐፍ ለግለሰቡ በስጦታ መልክ ስጠው።

እንዲያነብበው ጋብዘው።○ የሰጠኸው ሰው ወይም የሰጠኻት ሴት ጭምር የሌሎች ባሕርይ የሚያሰጋቸው ሆነው ልታገኛቸው ትችላለህ።

ስምህን ሳትጽፍ ለሰውየው የዚህን መጽሐፍ ተጨማሪ ቅጂዎች ስጥ። የሰጠኸው ሰው የራሱን ስም ይጽፍበታል። እርሱም እነዚህን ቅጂዎች የሕይወቱ ክፍል ለሆኑ ሌሎች ሰዎች እንዲሰጥ አድርገው።

ይህንን በማድረግ ከቀጠልክ የራስህንም ሆነ የነሱን ሕልውና በእጅጉ አስተማማኝ ማድረግ ትችላለህ።

ይህ አንተም ሆንክ ሌሎች ሰዎች ይበልጥ አስተማማኝና ደስተኛ ሕይወት እንድትመሩ የሚያስችል ጎዳና ነው።

○. ቃላት አንዳንድ ጊዜ የተለያየ ትርጉም ሊኖራቸው ይችላል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጠው የግርጌ ማስታወሻ ቃሉ በዚህ አገባቡ ያለውን ትርጉም የሚጠቁም ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የማታውቀው ቃል ካገኘህ ጥሩ መዝገበ ቃላት ተጠቅመህ ተመልከት። ይህንን ካላደረግህ አለመግባባቶች ወይም ክርክር የሚያስነሱ ጥያቄዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ።

ይህንን መጽሐፍ ለአንተ የሰጠሁበት ምክንያት

የአንተ ሕልውና[1] ለኔ አስፈላጊየ ነው።

ደስታ[2]

እውነተኛ ደስታና እርካታ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ነገሮች ናቸው።

አንድ ሰው ሕልውናውን ካጣ ደስታም ሆነ እርካታ የሚታሰቡ ነገሮች አይሆኑም።

ሁከትና[3] እምነት ማጉደል በሞላበት እንዲሁም በአጠቃላይ ሥነ ምግባር በጎደለው[4] ማሕበረሰብ ውስጥ ሕልውናን መጠበቅ አስቸጋሪ ነው።

ማንኛውም ግለሰብ ሆነ ቡድን ከሕይወት ማግኘት የሚችለውን ያህል ደስታ ለማግኘት ከመፈለጉም ሌላ ከስቃይ ነጻ የሆነ ሕይወት ለማግኘት ይናፍቃል።

በዙሪያህ ያሉ ሰዎች በሚያደርጉት መጥፎ ድርጊት ምክንያት ሕልውናህ አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል።

የሌሎች እምነት አጉዳይነትና አጉል ባሕርይ ደስታህን ሊያጠፋውና ወደ ኃዘን ሊለውጠው ይችላል።

እንዲህ ዓይነት አጋጣሚዎችን ልታስታውስ እንደምትችል እርግጠኛ ነኝ። እንዲህ ዓይነት ስህተቶች የአንድን ሰው ሕልውና የሚያሳጥሩና ደስታውን የሚያጨልሙ ናቸው።

---

1. ሕልውና፦ በሕይወት መቀጠል።
2. ደስታ፦ እርካታ፣ ደህንነት፣ ፍስሐ፣ ሐሴት፣ ያልታወከ ሕይወት፣ መልካም ነገር ሲያገኙ የሚታይ ተፈጥሮአዊ ምላሽ።
3. ሁከትና፦ አጠቃላይ ምስቅልቅል ወይም ግራ የሚያጋባ ሁኔታ።
4. ሥነ ምግባር የጎደለው፦ ብልግና፣ መልካም ምግባርን ያልተከተለ፣ ትክክል ያልሆነ ነገር፣ የጥሩ ምግባር ተቃራኒ።

አንተ ለሌሎች አስፈላጊ ነህ። ተደማጭነት አለህ። በጎ ተጽዕኖም ልታሳድር ትችላለህ።

የሌሎች የምታውቃቸው ሰዎች ደስተኛ መሆንና አለመሆን በአንተም ላይ የራሱ አንደምታ ይኖረዋል።

ያለ ብዙ ውጣ ውረድ ይህንን መጽሐፍ በመጠቀም ሕልውናቸውን አንዳያጡና ደስተኛ ሕይወት አንዲመሩ ልትረዳቸው ትችላለህ።

አንድም ሰው ስለ ሌላው ሰው ደስተኛ መሆን መቻል ሙሉ ዋስትና መስጠት ባይችልም ሕልውናውን የመጠበቅና ከእነርሱም የአንተም ሕልውናና ደስታ የማግኘት አጋጣሚ ይፈጥርልሃል።

አደጋ ያልበዛበትና የተሻለ ደስታ ያለበት ሕይወት ማግኘት የሚቻልበትን ጎዳና መጠቆም በእጅህ ነው።





I. ራስህን ጠብቅ

I-1. በምትታመምበት ጊዜ እርዳታ አግኝ።

ሰዎች ብዙውን ጊዜ ሲታመሙ አልፎ ተርፎም ተላላፊ በሽታ ይዟቸው እንኳን እያለ ከሌሎች ጋር ከመቀላቀል ወደ ኋላ አይሉም ወይም ተገቢውን ህክምና ለማግኘት አይሞክሩም። ይህም በቀላሉ መረዳት እንደምትችለው ሕይወትህን ለአደጋ ያጋልጠዋል። አንድ ሰው በሚታመምበት ጊዜ አግባብነት ያለውን የቅድሚያ ጥንቃቄ እንዲያደርግና ተገቢውን እንክብካቤ እንዲያገኝ አጥብቀህ አሳስብ።

I-2. አካላዊ ንፅህናህን ጠብቅ።

ገላቸውን ወይም እጃቸውን አዘውትረው የማይታጠቡ ሰዎች በአይን የማይታዩ በሽታ አስተላላፊ ህዋሳትን ሊሸከሙ ይችላሉ። እነዚህ ሰዎች አንተንም ለአደጋ ያጋልጡሃል። ሰዎች በየጊዜው ገላቸውንና እጃቸውን እንዲታጠቡ አጥብቀህ ማሳሰብህ ተገቢ ይሆናል። አንድ ሰው ሲሰራ ወይም ሲንቀሳቀስ መቆሸሹ አይቀርም። ከሰራ ወይም ከእንቅስቃሴ በኋላ እንዲታጠቡ አድርግ።

I-3. የጥርስህን ጤንነት ጠብቅ።

አንድ ሰው ምግብ በበላ ቁጥር ጥርሱን የሚቦርሽ ከሆነ የጥርስ ህመም እንደማያጋጥመው ይነገራል። ይህንን ማድረግ ወይም ምግብ ከተበላ በኋላ ሁልጊዜ ማስቲካ ማኘክ ሌሎችንም ከአፍ በሽታና ከመጥፎ የአፍ ጠረን ለመጠበቅ ያስችላል። ሌሎች ሰዎችም የጥርሳቸውን ጤንነት እንዲጠብቁ ሐሳብ ስጥ።

፤-4. ተገቢ አመጋገብ ይኑርህ።

በአግባቡ የማይመገቡ ሰዎች ለአንተም ሆነ ለራሳቸው አይበጁም። አቅማቸው አነስተኛ ነው። አንዳንድ ጊዜም ብስጩ ይሆናሉ። በቀላሉ ለበሽታ የሚጋለጡ ናቸው። በአግባቡ መመገብ ማለት የተለየ ምግብ መብላት ማለት ሳይሆን ገንቢ ምግቦችን አዘውትሮ መመገብ ማለት ነው።

፤-5. በቂ እረፍት አድርግ።

ብዙውን ጊዜ አንድ ሰው በሕይወት ዘመኑ የአንቅልፉን ጊዜ ሰውቶ ለመስራት የሚገደድባቸው ጊዜያት ቢኖሩም በአጠቃላይ ሲታይ አንድ ሰው ተገቢ እረፍት ሳያገኝ ከቀረ ለሌሎች ሸክም ሊሆን ይችላል። ድካም የተጫጫናቸው ሰዎች ንቁ አይደሉም። ስህተት ሊሰሩ ይችላሉ። አደጋ ያጋጥማቸዋል። ለስራ በሚፈለጉበት ወቅት የስራ ጫናው በሙሉ በአንድ ሰው ጫንቃ ላይ እንዲወድቅ ሊያደርጉ ይችላሉ። ሌሎችን ለችግር ያጋልጣሉ። በቂ እረፍት ያላደረጉ ሰዎች እረፍት እንዲያደርጉ አጥብቀህ አሳስብ።

2. ረጋ ያለ መንፈስ[5] ይኑርህ

2-1. ጎጂ የሆኑ አደንዛዥ ዕፆችን አትውሰድ።

አደንዛዥ ዕፆችን የሚወስዱ ሰዎች ሁልጊዜ ፊትለፊታቸው ያለውን የአለምን እውነታ ይሸሻሉ። *በእውነታው አለም* ውስጥ አይደሉም ያሉት። በአውራ ጎዳናም ላይ ሆነ በአጋጣሚ ወይም በቤት ውስጥ ብታገኛቸው እንደነዚህ አይነት ሰዎች በጣም አደገኛ ሊሆኑ ይችላሉ። ሰዎች "የተሻለ ስሜት የሚሰማቸው"፣ "የተሻለ ነገር ማከናወን የሚችሉት" ወይም "ደስታ የሚያገኙት" አደንዛዥ ዕፆችን ሲወስዱ ብቻ እንደሆነ አድርገው በተሳሳተ መንገድ ያስባሉ። ይህ ሌላው ራስን ማታለያ ነው። ፈጥኖም ይሁን ዘግይቶ አደንዛዥ ዕፁ አካላዊ ጉዳት ያደርስባቸዋል። ሰዎች አደንዛዥ ዕፅ እንደይወስዱ አድርጋቸው። እየወሰዱም ከሆነ ለመተው እገዛ እንዲያገኙ አበረታታቸው።

2-2. ከልክ በላይ አትጠጣ።

አልኮል የሚጠጡ ሰዎች ንቁ አይደሉም። አልኮል በመጠጣታቸው ምክንያት ይበልጥ ንቁ እንደሆኑ በሚሰማቸው ጊዜ እንኳን ሳይቀር አልኮሉ ለነገሮች ምላሽ የመስጠት ችሎታቸውን ያዛባባቸዋል። አልኮል በተወሰነ መጠን የመድሃኒትነት ጠቀሜታ አለው። ሆኖም ይህ ጠቀሜታው ከልክ በላይ ሊጋነን ይችላል። መጠጥ የጠጣ ማንኛውም ሰው በሚያሽከረክረው መኪና ወይም በሚያበርረው አውሮፕላን አትሳፈር። መጠጥ መጠጣት በብዙ አቅጣጫ ለህይወት መጥፋት ምክንያት ሊሆን ይችላል። ትንሽ የአልኮል መጠጥ ብዙ መዘዝ ሊያስከትል ይችላል። በመሆኑም ብዙ አልኮል በመውሰድ መጨረሻው የማያምር ወይም ሕይወት የሚጠፋበት ሁኔታ እንዲፈጠር አትፍቀድ። ሌሎች ሰዎች ከልክ በላይ እንዳይጠጡ ከልክል[6]።

አንድ ሰው በሕይወቱ ውስጥ ከላይ ያሉትን ነጥሞች ከሰራባቸው አካላዊ ጥንካሬ ሰለሚያገኝ ሕይወቱ ደስተኛ ይሆናል።

5. ረጋ ያለ መንፈስ፦ ወደ ሌላኛው ጽንፍ አለመሄድ፣ ነገርን በልኩ ማድረግ፣ የራስን ምኞት መቆጣጠር።

6. ከልክል፦ አንዳያደርጉት ተቃወም።

3. ሴሰኛ[7] አትሁን

ወሲብ የአንድ ሰው የዘር ሃረግ ልጆች በመውለድና ቤተሰብ በማፍራት እየተባዛ መቀጠል የሚችልበት መንገድ ነው። ከወሲብ ብዙ ደስታ ሊገኝ ይችላል። ይህ ሁኔታ የሰው ዘር እየተባዛ እንዲቀጥል ተፈጥሮ ራሷ ያመቻቸችው አሠራር ነው። ይሁን እንጂ አላግባብ ጥቅም ላይ ከዋለ ከባድ የቅጣት ጅራፉን ሊያሳርፍ ይችላል። እንደ ደስታው ሁሉ ቅጣቱም ተፈጥሮ ያመቻቸችው ይመስላል።

3-1. ለወሲብ ጓደኛህ ታማኝ ሁን።

ለወሲብ ጓደኛ ታማኝ አለመሆን ሕይወትን በአጭር ለሚቀጭ አደጋ በእጅጉ ያጋልጣል። ከታማኝነት ጉድለት የሚመነጩና በስሜት ግፊት የሚፈፀሙ ዓመጾችን በተመለከተ ከታሪክም ሆነ ከጋዜጣ ገጾች ላይ ብዙ መማር ይቻላል። "የጥፋተኝነት ስሜት" ራሱን የቻለ ከባድ ሸክም ነው። ቅንዓትና በቀል ደግሞ ይባስ የከፋ ናቸው። እነዚህ ባሕርያት በአንድ ሰው ውስጥ መቼ እንደሚገነፍሉ አይታወቅም። ስለሆነም "የሰለጠኑ" ብሎም "ግልጽና" "የሌሎችን ስሜት የሚረዱ" ሰዎች ስለመሆን ማሰባችን ተገቢ ይሆናል። ሆኖም በአንድ ሰው ህይወት ውስጥ የደረሰውን ጉዳት ሊጠግን የሚችል ምንም ዓይነት ቃል አይኖርም። የጥፋተኝነት ስሜት የሚያስከትለው ስቃይ ከጀርባ በስለታም ቢላዋ ከመወጋት ወይም ከሾርባ ጋር የብርጭቆ ስብርባሪ ከመዋጥ ፈጽሞ የከፋ ነው።

በተጨማሪም የጤና ጉዳይ አለ። የወሲብ ጓደኛህ/ሽ ታማኝ እንድትሆን/እንዲሆን የማታሳስብ/የማታሳስቢ ከሆነ ለበሽታ መጋለጥን ያስከትላል። ለተወሰነ ጊዜ በጾታ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል ተብሎ ነበር። በወቅቱ ውጤት ተገኝቶ የነበረ ሊሆን ቢችልም እንኳ አሁን ሁኔታው

7. ሴሰኛ፦ በተገኘው አጋጣሚ የጾታ ግንኙነት የሚፈጽም።

ተለውጧል። በዛሬው ጊዜ ዕፅ የሌላቸው በወሲብ ምክንያት የሚተላለፉ በሽታዎች አሉ።

የሴሰኝነት ባህርይ የሚያስከትላቸው ችግሮች እንግዳ ነገሮች አይደሉም። በሕንድ የሚገኘው ታላቁ የቡድሂዝም ሃይማኖት በሰባተኛው መቶ ዘመን ከዚያ አገር ጠፍቶ ነበር። ከሃይማኖቱ ታሪክ ጸሐፊዎች መረዳት እንደሚቻለው ምክንያቱ በገዳማቱ ይፈጸም የነበረው የሴሰኝነት ድርጊት ነው። በዘመናችን ያለውን ሁኔታ ስናይ ደግሞ በአንድ የንግድ ድርጅት ወይም በሌላ ተቋም ውስጥ በሴሰኝነት ምክንያት ድርጅቱ ወይም ተቋሙ ሲወድቅ ይታያል። ቤተሰሞች ስለ ጉዳዩ የቱንም ያህል በሰለጠነ መንገድ ቢወያዩ ታማኝነታቸውን አስካልጠበቁ ድረስ ቤተሰቡ ከመፍረስ አይድንም።

ጊዜያዊ የስሜት ግፊት የዕድሜ ልክ ሐዘን ውስጥ ሊከትት ይችላል። በዚህ ረገድ በዙሪያህ ላሉ ሰዎች በግልጽ የሚታይ ጠንካራ አቋም በመያዝ ጤናህንና ደስታህን ጠብቀህ ኑር።

መሲብ ደስታና የስሜት እርካታ ሊያሰገኝ የሚችል ትልቅ እርምጃ ነው። በታማኝነትና በጨዋነት ከተጠቀምንበት በራሱ ሰህተት አይደለም።

4. ሕፃናትን አፍቅር እርዳቸውም

የዛሬ ሕፃናትየነገው ስልጣኔ ተረካቢ ናቸው። ዛሬ አንድን ሕፃን ወደዚህ ዓለም ማምጣት በጥቂቱም ቢሆን አንድን ሰው የነብር ዋሻ ውስጥ ከመጣል ጋር ሊወዳደር ይችላል። ሕፃናት በአካባቢያቸው[8] ያለውን ሁኔታ ማስተናገድ የሚችሉበት ምንም አቅም የላቸውም። ይህንን ማድረግ እንዲችሉ ፍቅርና እርዳታ ያስፈልጋቸዋል።

ይህ ለመወያያዬት የማይመች ርዕስ ነው። አንድን ልጅ ስናሳድግ ምን ማድረግ አለብን? ምንስ ማድረግ የለብንም? የሚሉት ንድፈ ሐሳሞች ብዛት በወላጆች ቁጥር ልክ ነው። ይሁንና አንድ ሰው በዚህ ረገድ የሚወስደው የተሳሳተ እርምጃ ብዙ ሃዘን ሊያስከትልና የራሱን የኋለኛ ሕይወት ጭምር ሊያወሳስብበት ይችላል። አንዳንዶች ልጆችን ለማሳደግ የሚሞክሩት ራሳቸው ባደጉበት መንገድ ነው። ሌሎች ደግሞ ተቃራኒውን ሲሞክሩ ብዙዎች ደግሞ ልጆች በራሳቸው መንገድ እንዲያድጉ ሊተዉ ይገባል የሚል እምነት አላቸው። ከእነዚህ አካሄዶች መካከል ማናቸውም ቢሆኑ ለስኬት ዋስትና የላቸውም። የመጨረሻው አማራጭ ቁስ-አካላዊ[9] አስተሳሰብ ነው። ይህም ከልጁ ዝርያ የአዝጋሚ ለውጥ[10] ታሪክ ጋር የሚነጻፀር ነው በሚል እምነት ላይ የተመሰረተ ነው። በዚህ መሰረት ምትሀታዊ በሆነና ሊብራራ በማይችል መንገድ ልጁ እያደገ ሲሄድ የልጁ "ነርቭ እየበሰለ" ሄዶ በጥሩ ምግባር[11]

---

8. በአካባቢያቸው፦ በዙሪያችን ያለ ቦታ፣ በዙሪያህ የሚገኝ ቁሳዊ ነገር፣ አንድ ሰው የሚኖርበት ቦታ፣ አንድ ሰው በቅርብም ይሁን በሩቅ የሚያገኛቸው ሕይወት ያላቸውና ግዑዛን ነገሮች፣ ቦታዎች እና ኃይሎች።

9. ቁስ-አካላዊ፦ ቁስድአካል ብቻ ነው ያለው የሚል እምነት።

10. አዝጋሚ ለውጥ፦ ሁሉም አጽዋትና እንስሳት ከትንሽ ነገር ተነስተው ቀስ በቀስ በመሻሻልና እና በአካባባያቸው በመቀረጽ እንጂ በዕቅድ ወይም ተፈጥረው አልተገኙም የሚል ጥንታዊ ንድፈ ሐሳብ።

11. ምግባር፦ ትክክል እና ስህተት የሆነውን መለየት መቻል፤ ከዚህ ግንዛቤ ተነስቶ እርምጃ መውሰድ።

የታኔና ክፋና ደጉን የሚለይ ጎልማሳ እንዲሆን ይረዳዋል ተብሎ ይታመናል። ብስለት በጎደላቸው ብዙ ወንጀለኞች ምሳሌ ብቻ ይህ ንድፈ ሃሳብ ስህተት መሆኑን በቀላሉ ማረጋገጥ የሚቻል ቢሆንም ልጆችን በማሳደግ የተወሰነ እውቅና ለማግኘት መጣር የሞኝነት አካሄድ ነው። የወደፊቱን ስልጣኔም ሆነ የኋለኛውን አድሜህን ያላገናዘበ ነው።

አንድ ሕፃን በተወሰነ መጠን ከባዶ ወረቀት ጋር ሊነፃፀር ይችላል። የተሳሳተ ነገር ከፃፍክበት የሚያነበውም የተሳሳተ ነገር ነው። ይሁን እንጂ ሕፃኑ ከወረቀቱ በተለየ መልኩ ራሱ መፃፍም ይጀምራል። የሚፅፈው ደግሞ መጀመሪያውኑ የተፃፈለትን ነው። ችግሩን ውስብስብ የሚያደርገው ደግሞ ብዙ ልጆች ከፍተኛ የጨዋነት አቅም እያላቸው ጥቂቶች ዛሬ ዛሬ ወፈፍ የሚያደርጋቸዉ አብድ አንዳንዶች ደግሞ የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኛ ሆነው መወለዳቸው ነው። ይሁን እንጂ የእንዲህ አይነቶቹ ልጆች ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው።

ሕፃንን የአሻንጉሊቶች ስጠታ እና ሌሎች ነገሮች “እየገዙ” ማጥለቅለቅ ወይም ከስር ከስሩ እየተከተሉ መንከባከብ ብቻውን የሚፈይደው ነገር የለም። ውጤቱ አሳዛኝ ሊሆን ይችላል።

አንድ ሰው ልጁ ምን ዓይነት ሰው እንዲሆን እየጣርኩ ነው በማለት ቆም ብሎ ራሱን መጠየቅ ይኖርበታል። ለዚህ ውጤት ድርሻ የሚኖራቸው ነገሮች አሉ፤ ሀ) ሕፃንከወረሰው ተፈጥሮአዊ ባህርይ አንፃር ሊሆን *ዮሚ ችለው* ነገር፣ ለ) ሕፃኑ ራሱ መሆን የሚፈልገው ነገር፣ ሐ) ሌላው ሰው ሕፃኑ መሆን አለበት ብሎ የሚያስበው ነገር እንዲሁም መ) ያለው የቁሳቁስ፣ የእሴት እና የሀብት መጠን ናቸው። ሆኖም ይህ ሁሉ ነገር እያለም ልጁ በራሱ የሚመራና *ከፍተኛ* የሥነ ምግባር ሰው ካልሆነ በቀር በቅጡ ሊዘልቅ *እንደሚይችል* ማስታወስ ይገባል። አለዚያ ግን የመጨረሻው ውጤት ሕፃኑን ራሱን ጨምሮ ሁሉንም ችግር ላይ እንደሚጥል የታወቀ ነው።

አንድ ሰው ለሕፃን ያለው ፍቅር የቱንም ያህል የጠለቀ ቢሆን ሕፃኑ በህልውና ጎዳና በሁለት እግሩ መቆም አስካልቻለ

ድረስ ጥሩ ህይወት ሊኖር እንደማይችል ማስታወስ ያስፈልጋል። ሕፃኑ በተሳሳተ ጎዳና ላይ ቢገኝ እንደ ድንገተኛ ክስተት መታየት የለበትም፤ በዙሪያው ያለው ማህበረሰብ ሕፃናትን ወደ ውድቀት ለመውሰድ ምቹ ሆኖ የተዘጋጀ ነው።

ሕፃኑ የዚህን መፅሐፍ መሰረታዊ መመሪያዎች[12] በተመለከተ ያለውን መረዳት እና የሚስማማባቸው መሆኑን መገንዘብ መቻል ከፍተኛ እገዛ ይኖረዋል።

ጥሩ ውጤት የሚያመጣው ነገር ሕፃኑን ወዳጅ ማድረግ ነው። አንድ ሕፃን ጓደኞች እንደሚያስፈልጉት የታወቀ ነው። የሕፃን ልጅ እውነተኛ ችግር ምን እንደሆነ ለማወቅ ሞክሩ። ከዚያም እርሱ የሚያቀርበውን መፍትሄ ሳታጣጥሉ ችግሩን እንዲፈታ እርዱት። ሕፃናትን በቅርብ ማስተዋል ያስፈልጋል። ይህ ትናንሽ ህፃናትንም ይጨምራል። ሕፃናት ስለ ራሳቸው የሚናገሩትን አዳምጧቸው። የበኩላቸውን አስተዋፅኦም እንዲያበረክቱም *ፍቀዱላቸው*። አለበለዚያ አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ በሚል የሃላፊነት[13] ስሜት ስለሚዋጡ ይህንን ስሜት በውስጣቸው አምቀው ለመያዝ ይገደዳሉ።

አንድ ሕፃን ደስታ ለማግኘት የሚያስችለውን ጎዳና በተመለከተ ያለውን መረዳትና የሚስማማበት መሆኑን በመገንዘብ በዚህ ጎዳና እንዲሄድ መርዳት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ይህ በእናንተም ሆነ በሕፃኑ ህልውና ላይ ከፍተናፎ ውጤት ይኖረዋል።

እንደ እውነቱ ከሆነ ሕፃን የግድ ፍቅር ማግኘት ይኖርበታል። አብዛኞቹ ሕፃናት ደግሞ ለምናሳያቸው ፍቅር በእጥፍ ምላሽ መስጠት ይችላሉ።

ወደ ደስታ የሚመራው ጎዳና ሕፃናትን ከልጅነት እሰከ እውቀት በፍቅር መያዝና ማገዝን ያበረታታል።

---

12. መመሪያዎች፦ የእንድን ሰው እኗኗር የሚመሩ መሠረታዊ መመሪያዎችን ለማስቀመጥ የሚረዱ ደንቦች ወይም ሐሳቦች፣ የእኗኗር መመሪያ እንዲሆኑ የታሰቡ ደንቦች።

13. ኃላፊነት፦ በአንድ የውስጣ ድርጊት፣ በተሰጠ አገልግሎት ምክንያት ለሌላው ባለ ዕዳ መሆን።

5. ወላጆችህን አክብር[14] አግዛቸውም

አንዳንድ ጊዜ ልጆች ወላጆቻቸውን መረዳት ያስቸግራቸዋል። በትውልዶች መካከል የሚፈጠር ልዩነት አለ። ይሁንና እውነቱን ለመናገር ይህ ጋሬጣ አይሆንም። አኑ የራሱን ድክመት ለመሸፈን ማታለያ ዘዴ ፈጥሮ ይዋሻል። በሁለቱ ትውልድ መካከል ግድግዳ የሚሆነው ይህ ነው።

ልጆች ከወላጆቻቸው ጋር ያላቸውን አለመግባባት ማስታረቅ ይችላሉ። መጫጫህ ከመጀመሩ በፊት አንዳቸው በዝግታ ጉዳዩን አንስተው ለመወያየት ሊሞክሩ ይችላሉ። ልጁ ግልፅና ሃቀኛ ከሆነ ጥሩ ውጤት ይገኛል። ብዙውን ጊዜ ሁለቱም ወገኖች በስሜት ከተግባቡና መስማማት ከቻሉ በየበኩላቸው ማስተካከያ[15] ማድረግ ይችላሉ። ከሌሎች ጋር ተግባብቶ መዝለቅ ሁልጊዜ ቀላል አይሆንም። ሆኖም አንድ ሰው የበኩሉን ጥረት ማድረግ አለበት።

ወላጆች ሁልጊዜ ማለት ይቻላል አንድ ነገር የሚያደርጉት ልጆቻቸውን ለመጥቀም ካላቸው ጠንካራ ፍላጎት ተነሳስተው መሆኑን መዘንጋት አይኖርብንም።

ልጆች ወላጆቻቸው ስላሳደጓቸው የእነርሱ ባለ እዳ ናቸው። አንዳንድ ወላጆች ከሌላ ሰው ምንም የማይጠብቁ በመሆናቸው ግዴታቸውን ስለተወጡ ብቻ በምላሹ የሆነ ነገር እንዲደረግላቸው አይጠብቁም። የሆነ ሆኖ ብዙውን ጊዜ ወጣቶች በተራቸው ወላጆቻቸውን እንደንከባከቡ የሚያስፈልግበትጊዜ ይመጣል።

---

14. አክብር፦ ከፍ ያለ ግምት መስጠት፣ የተለየ አያያዝ ማድረግ።
15. ማስተካካያ፦ አያንዳንዱ ወገን አንዱን ነገር ይዞ ሌላውን በመተው የጋራ ስምምነት ላይ ደርሶ አለመግባባትን ለመፍታት የሚችልበት አርምጃ።

ከሁሉም በላይ ግን አንድ ልጅ ከወላጆቹ ሌላ ወላጅ
አንደሌለው ማስታወስ አለበት። በመሆኑም ሁኔታው ምንም
ይሁን ምን ልጁ ወላጆቹን ሊያከብራቸውና ሊረዳቸው ይገባል።

ወደ ደስታ የሚመራው ጎዳና ከወላጆች ወይም ከአሳዳጊዎች
ጋር መግባባትን ይጨምራል።



6. ጥሩ ምሳሌ[16] ሁን

አንድ ሰው በብዙ ሰዎች ላይ ተፅእኖ[17] ያሳድራል። ተፅእኖው[18] በጎም መጥፎም ሊሆን ይችላል።

አንድ ሰው በዚህ ጽሁፍ ላይ የተሰጡትን አስተያየቶች ተግባራዊ የሚያደርግ ከሆነ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል።

በዙሪያው ያሉ ሌሎች ሰዎች በአንደበታቸው የሚናገሩት ምንም ይሁን ምን በእርሱ ተፅእኖ መነካታቸው አይቀርም።

ተስፋ ሊያስቆርጡህ የሚሞክሩ ካሉ ይህንን የሚያደርጉት በተዘዋዋሪ ድርጊትህ አንዳበሳጫቸው ለመግለጽ ወይም የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ በማሰብ ሊሆን ይችላል። በውስጣቸው ግን ያከብሩሃል።

አንተ ተፅእኖ ያሳደርክባቸው ሰዎች የሚያሳድሩት ስጋት ስለሚቀንስ የአንተም በህልውና የመቆየት አጋጣሚ ይሻሻላል። ሌሎች ጥቅሞችም አሉ።

እነዚህን ነገሮች ለሌሎች በመንገርና መልካም ምሳሌ በመሆን በሌሎች ላይ ልታሳድር የምትችለውን ተጽእኖ አቅልለህ አትመልከተው።

ወደ ደሰታ የሚመራው ጎዳና ለሌሎች ምሳሌ መሆንን ይጠይቃል።

16. ምሳሌ፦ ሊኮረጅ የሚገባው ሰው ወይም ነገር፤ ናሙና።
17. ተፅእኖ፦ በሌላው ሰው ላይ ውጤት የሚያስከትል ነገር።
18. ተፅእኖው፦ ያስከተለው ውጤት።

7. እውነትን[19] ይዘህ ለመኖር ጥረት አድርግ

የሃሰት መረጃ አንድ ሰው ጥበብ የጎደለው እርምጃ እንዲወስድ ሊያደርግ ይችላል። እውነተኛ መረጃንም አንዳይቀበል ሊያደርገው ይችላል።

አንድ ሰው በህይወቱ የሚገጥመውን ችግር መወጣት የሚችለው እውነተኛ መረጃ ሲኖረው ብቻ ነው።

ሰዎች ለአንድ ሰው ውሸት ከነገሩት ያ ሰው በዚያ ተመርቶ ስህተት ሊሠራና ይህም ህልውናውን ሊቀጭበት ይችላል።

የተሳሳተ መረጃ ከተለያዩ ምንጮች ሊገኝ ይችላል። ከእነዚህም መካከል ትምህርት ቤት፣ ማህበራዊ ተቋም እና ባለሙያዎች ይገኙበታል።

ብዙ ሰዎች የራሳቸው የግል ግብ ለማሳካት ሲሉ ብቻ አንዳንድ ነገሮችን አንድታምንላቸው ይፈልጋሉ።

እውነት የሚባለው *ለአንተ* እውነት የሆነው ነገር ነው።

ማንም ሰው አንድ የሆነ መረጃን እንድትቀበል ሊያስገድድህ ወይም እንድታምንበት ሊያዝህ አይችልም። ለአንተ እውነት ካልሆነ እውነት አይደለም።

በራስህ መንገድ አስብ፤ ለአንተ አውነት የሆነውን ተቀበል። ሌላውን አትቀበል። በሃሰት[20] ተተብትሞ ለመኖር ከመሞከር የከፋ ደስታን የሚያሳጣ ነገር የለም።

---

19. እውነት፦ ከእውነታውና ከሚታየው ነገር ጋር የሚስማማ፣ እውነታዎችንና መረጃዎችን በማገላበጥ የሚገኝ ተጨባጭ መልስ፤ በፍላጎት፣ በሥልጣን ወይም በስሜታዊነት ያልተዛባ፣ በመረጃ ላይ የተመሰረተ መደምደሚያ፤ በምንም መንገድ ይታወቅ ሊሻር የማይችል ሐቅ።

20. በሃሰት፦ ሆን ተብሎ አውነት እንደሆነ ተደርጎ የሚቀርብ የተሳሳተ መረጃ፤ ውሸት የሆነ ነገር፤ ለማታለል ወይም የተሳሳተ አመለካከት ለመቅረጽ የታሰበ ነገር።

7-1. ጎጂ ሀሰት አትናገር።

ጎጂ ውሸቶች የፍርሃት፣ የጥላቻ፣ እና የቅንዓት ውጤቶች ናቸው። ሰዎችን የተሰፋ መቁረጥ እርምጃ እንዲወስዱ ሊገፋፉ ይችላሉ። የሰውን ህይወት ሊያሳጡ ይችላሉ። ውሸት ተናጋሪውም ሆነ የውሸቱ ሰለባ የሆነው ሰው የሚገቡበትን ጉድጓድ ሊምሱለት ይችላሉ። በግለሰሞች መካከልም ሆነ በማህበረሰብ ውስጥ ቀውስ ሊፈጥሩ ይችላሉ። በጎጂ ውሸቶች ምክንያት ብዙ ጦርነቶች ተቀስቅሰዋል።

አንድ ሰው እነዚህን ሀሰቶች ለይቶ ማወቅና ወደ ጎን ገሸሽ ማድረግን መማር ይኖርበታል።

7-2. የሐሰት ምስክርነት አትስጥ።

እውነት ያልሆኑ "መረጃዎችን" በተመለከተ ከመማል ወይም ምስክርነት ከመስጠት ጋር የተያያዙ ብዙ ቅጣቶች አሉ። እንዲህ ያለው ሁኔታ "ቅድመ ዳኝነት" ይባላል። ከባድ ቅጣት ያስከትላል።

ወደ ደሰታ የሚመራው ጎዳና
የእውነት ጎዳና ነው።



8. አትግደል[21]

አብዛኖፎቹ የሰዉ ዘርያወች ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ነፍስ ግድያን ሲከለክሉና ይህንኑ በሚያደርጉ ላይ ከፍተኛ ቅጣት ሲበይኑ ኖረዋል። አንዳንድ ጊዜ ይህ ትእዛዝ ሰፋ ያለ ትርጉም በሚያስተላልፍ መልኩ "ህይወት ማጥፋት" አይኖርብህም ተብሎ ተቀምጧል። ከጊዜ በኋላ የተሰራ ሌላ ትርጉም "አትግደል" ሲል አስቀምጠታል።

መግደል እና *ህይወት ማጥፋት* በሚሉት ሁለት ቃላት መካከል ሰፊ ልዩነት አለ። ህይወት ማጥፋት የለብህም የሚለው ገደብ ራስህን መከላከል የለብህም ማለትም ሊሆን ይችላል። ይህ አንድን ልጅ ለመንደፍ እያደባ ያለውን እባብን መከላከልንም ህገወጥ ያደርገዋል። አንድ ዘር ከቅጠላ ቅጠል ውጭ አንዳይመገብም የሚከለክል ይሆናል። ሕይወት ማጥፋት የለብህም የሚለው ገደብ የሚያስከትላቸውን ችግሮች በተመለከተ አንተም ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ እንደምትችል እርግጠኛ ነኝ።

መግደል ደግሞ ከዚህ ፈፅሞ የተለየ ነገር ነው። ጥሬ ፍቺው እንደሚከተለው ይሆናል፤ "በጥላቻ ተነሳስቶ ህገወጥ በሆነ መንገድ የአንድን ሰው ወይም የብዙ ሰዎችን ህይወት ማጥፋት።" ብዙ የአመፅ መሳሪያዎች ባሉበት በዚህ ዘመን ነፍስ ግድያ ምን ያህል ቀላል እንደሆነ መገመት ለማንም አያዳግትም። የራሳችንም ሆነ የቤተሰባችን አባላት ህይወት የሚተርፈው የሰዎችን ህይወት በዘፈቀደ በሚቀጥፉ ሰዎች በጎ ፈቃድ ብቻ በሆነበት ህብረተሰብ ውስጥ መኖር ከባድ ነው።

ነፍስ ግድያ ማህበረሰቡ ሊከላከላቸው ወይም ለፍርድ ሊያቀርባቸው ከሚገባው ነገሮች መካከል ቀዳሚውን ስፍራ መያዙ እጅግ የተገባ ነው።

---

21. አትግደል፦ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ በተለይም በጥላቻ ተነሳስቶ (አስቀድሞ አስቦበት) የሌላውን ሰው (ሰዎች) ሕይወት ማጥፋት።

ሰነፍ፣ ክፋ እና አእምሮውን የሳተ ሰው ያጋጠመውንም ሆነ ያጋጥመኛል ብሎ የሚያስበውን ችግር የሚፈታው ነፍስ በማጥፋት ነው። እንደነዚህ አይነት ሰወች ያለምንም ምክንያትም ይህንኑ ድርጊት እንደሚፈፅሙ ይታወቃል።

ይህንን የሰው ዘር ስጋት ላይ የማጥል ድርገት ለመከላከል የተቋቋመ ውጤታማ ፕሮግራም ካለ ድጋፍህን ስጥ። የአንተም ሕልውና በዚሁ ላይ የተመካ ሊሆን ይችላል።

ወደ ደሰታ የሚመራው ጎዳና ወዳጆችህን፣ ቤተሰሞቸህን ወይም ራስህን መግደልን አይጨምርም።



9. ህገወጥ የሆነ ማንኛውንም ዓይነት ተግባር አትፈፅም

ህገወጥ የሚባሉት ተግባራት በኦፊሴላዊ ደንብ ወይም ህግ የተከለከሉ ድርጊቶች ናቸው።

ብዙውን ጊዜ በገዥዎች፣ በህግ አውጪ አካላት እና በዳኞች በህግ መልክ የሚዘጋጁም ናቸው። በሚገባ በተደራጀ ማህበረሰብ ውስጥ እነዚህ ህግጋት በፅሁፍ ታትመው ህዝብ በትክክል እንዲያውቃቸው ይደረጋል። የተሸፋፈነ አሠራር ባለበትና ወንጀል በበዛበት ህብረተሰብ ውስጥ እነዚህን ህጎች በሙሉ ለማወቅ የህግ ባለሙያ ማማከር ወይም የተለየ ስልጠና መውሰድ ያስፈልጋል። እንዲህ ባለ ማህበረሰብ ውስጥ "አለማወቅ ህግን ለመጣስ ምክንያት አይሆንም።

ይሁን እንጂ ማንኛውም የማህበረሰቡ አባል ወጣት አረጋዊ ሳይል በማህበረሰቡ ውስጥ "ህገወጥ" የሚባሉትን ነገሮች ለይቶ የማወቅ ሃላፊነት አለበት። ሰዎችን መጠየቅ ይቻላል፣ አለዚያም መጽሀፍትን ማገላበጥ የሚቻልባቸው ቤተ መፃህፍት ይኖራሉ።

"ህገወጥ" ድርጊት የሚባለው "መተኛት አለብህ" የሚለውን አይነት የተለመደ ትእዛዝ የመጣስ ተግባር አይደለም። ሕገ ወጥ ድርጊት ከተፈፀመ በፍርድ ቤት እና በመንግስት አካል ለቅጣት የሚዳርግ፣ በመንግስት መገናኛ ብዙሃን በሚነዛው ፕሮፓጋንዳ[22] በይፋ መዘባበቻ[23] የሚያደርግ ብሎም በጥፋተኛነት ለመቀጣትና የገንዘብ ወይም የእስር ብይን ለመቀበል የሚያስገድድ ተግባር ነው።

---

22. ፕሮፓጋንዳ፦ የራስህን ሐሳብ ለማስፋፋት እና/ወይም ሌላውን ለመጉዳት ሲባል የሚሰራጭ ሐሳብ፣ መረጃ ወይም ወሬ፤ ብዙውን ጊዜ እውነት ስለመሆኑ ሳይታሰብበት የሚነገር፤ የሐሰት መረጃዎችን በሕትመት ውጤቶች፣ በቴሌቪዥን ወይም በሬድዮ በማውጣት አንድን ግለሰብ ጥፋተኛ ማድረግ፣ በሐሰት የአንዳን ሰው ስም በማጥፋት ተደማጭነት አንዳያገኝ ማድረግ። የፕሮፓጋንዳ አቀንቃኝ፦ ፕሮፓጋንዳ መንዛቱን ሥራው ያደረገ ግለሰብ ወይም ቡድን።

23. መዘባበቻ፦ ለፌዝ፣ ለሕዝብ መሳለቂያነት ወይም ማላገጫነት መጋለጥ።

ብዙውን ጊዜ አንድ ሰው ህገወጥ ተግባር ሲፈጽም የፈፀመው ተግባር ትንሽም ሆነ ትልቅ በመንግስት እጅ ላይ ወደቀ ማለት ነው። አንድ ሰው ህገወጥ ተግባር ከፈፀመ ተያዘም አልተያዘ ራሱን ለችግር አጋልጧል።

አንድ ሰው ለማድረግ የሚጥረው ማንኛውም ጠቃሚ ተግባር በሙሉ ለማለት ይቻላል ፍፁም ህጋዊ በሆነ መንገድ ሊከናወን ይችላል። "ህገወጥ" የሆነው አካሄድ በጣም አደገኛና ጊዜ የሚወስድ አቋራጭ ነው። ህገወጥ ተግባር በመፈፀም ይገኛሉ ተብለው የሚታሰቡት "ጥቅሞች" ብዙውን ጊዜ ውጤታቸው በተቃራኒው የከፋ ነው።

መንግስትና መስተዳደሮች የሚያስብ ማሽን መሆን ይቀናቸዋል። የህልውናቸውም ሆነ የስራቸው መሰረት ህግና ደንብ ነው። ህገወጥነትን በራሳቸው መዋቅር አማካኝነት ለመቅጨት የተቃኙ ናቸው። ከዚህ አንፃር ሲታይ የማያባብሉት[24] ጠላትና "ህገወጥነትን" የማይታገስ የጋሪ ፈረስ[25] ሆነው ይገኛሉ። በህግና ደንብ ፊት የአንድ ነገር ትክክል ወይም ስህተት መሆን ብቻውን ዋጋ የለውም። ወሳኙ ነገር ህጉ ነው።

በዙሪያህ ያሉ ሰዎች "ህገወጥ" ተግባር እየፈፀሙ መሆናቸውን ከተገነዘብክ ከዚህ ተግባራቸው እንዲታቀቡ የቻልከውን ያህል ጥረት ማድረግ ይኖርብሃል። አንተ ራስህ የጥፋቱ ተካፋይ ባትሆንም እንኳ የችግሩ ሰለባ ልትሆን ትችላለህ። የአንድ ድርጅት ሂሳብ ሰራተኛ ሂሳቡን አጭበርብሯል እንበል። በዚህ ምክንያት በሚፈጠረው ችግር ድርጅቱ ሊከስርና አንተም ከስራ ልትፈናቀል ትችላለህ። እንዲህ ዓይነቶቹ ሁኔታዎች የአንድን ሰው ህልውና በእጅጉ ሊጎዱ ይችላሉ።

ለህግ ተገዥ የሆነ የአንድ ቡድን አባል ከሆንክ እነዚህ ህጎች ይታወቁ ዘንድ ህግጋቱ በግልፅ ታትመው እንዲወጡ አበረታታ። አንተ አባል የሆንክበትን ቡድን የሚመለከቱ ህግጋት እንዲቀነሱ፣

---

24. የማያባብሉት፦ ለማግባባት፣ ለማስደሰት የማይመች፣ ምህረት የለሽ፣ ግትር።
25. የጋሪ ፈረስ፦ ግትር፣ የማይታጠፍ፣ ችኮ፣ ሌላ ሐሳብ ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆነ።

ግልጽ እንዲሆኑና በህግ መልክ እንዲወጡ የሚደረገውን የህግና የፖለቲካ ጥረት ደግፍ። ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው የሚለውን መርህ አጥብቀህ ተከተል። ይህ መርህ በራሱ ጊዜና ሞታ ማለትም በፈላጭ ቆራጭ[26] ፊውዳላዊ[27] ዘመን እንደ ታላቅ ማህበራዊ እመርታ የታየበት ጊዜ ስለነበር ሊዘነጋ አይገባም።

ልጆችም ሆኑ ሌሎች ሰዎች "ህጋዊ" እና "ህገወጥ" የሆኑትን ነገሮች እንዲያውቁ አድርግ። "ህገወጥ ድርጊቶችን" ቅንጣት ታክል እንኳ እንደማትደግፍ አሳይ።

ወደ ደስታ የሚመራው ጎዳና ላይ እያዝ ይሆን? ከሚል ፍርሃት ጋር መጓዝ አይታሰብም።



26. ፈላጭ ቆራጭ፦ ያለውን ሥልጣን በጭካኔና ፍትሕ በጎደለው መንገድ የሚጠቀም፣ ጨቋኝ።

27. ፊውዳላዊ፦ የተለየ መብት፣ ማዕረግና ሥልጣን ያላቸው ጥቂቶች የሚያስተዳድሩት መንግሥት፤ ከሕግ በላይ የሆኑ ጥቂቶች የሚያስተዳዳሩት፣ በውልደት ወይም በስልጣን ከሌሎች ሁሉ የሚበልጡ ተደርገው የሚታሰቡ እና አራሳቸው አንደ ሕግ የሚታዩ ሰዎች የሚገዙበት መንግሥት።



IO. ሰውን ሁሉ ለማገልገል የቆመንና ለዚሁ አላማ የሚንቀሳቀስን መንግስት ደግፍ

ይሉኝታ የሌላቸውና ክፋ ሰዎች ብሎም ቡድኖች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ የመንግስትን ስልጣን በእጃቸው ያስገባሉ።

የራሳቸውን ጥቅም ለማሟላት የቆሙ ግለሰሞችና ቡድኖች ፍላጎት ማስፈፀሚያ ብቻ የሆነ መንግስት የህብረተሰቡን የእድሜ ጣሪያ ያሳጥራል። ይህ ደግሞ የአገሪቱን ነዋሪዎች ህልውና የሚቀጭ ነው። አልፎ ተርፎም ወንበሩን ለመያዝ የሚሞክሩትን ወገኖች ጭምር የሚጎዳ ነው። ታሪክ በእንዲህ መሰሎቹ የመንግስታት ህልፈት የተሞላ ነው።

እንዲህ ዓይነት መንግስታትን መቃወም ብዙውን ጊዜ ተጨማሪ ዓመፅን ያስከትላል።

ሆኖም እነዚህን ኢ-ፍትሃዊ ተግባራት በመቃወም በጥንቃቄ ድምጽን ማሰማት ይቻላል። አንድ ሰው ህገወጥ የሆነ ተግባር መፈፀም ሳያስፈልገው ለእንዲህ ዓይነቱ መንግስት ድጋፍ ከመስጠት በመቆጠብ ብቻ የኋላ ኋላ ተሃድሶ ማምጣት ይችላል። ይህ ፅሁፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ እንኳን በዓለማችን ላይ ህዝባቸው ባለመተባበሩና በዝምታ ተቃውሞውን በመግለፁ ብቻ የሚወድቁ መንግስታት አሉ። እነዚህ መንግስታት ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠዋል። ባልተጠበቀ ወቅት የሚገነፍል ማንኛውም የተቃውሞ ማእበል ጠራርጎ ሊወስዳቸው ይችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ለመላው ህዝቡ ጠንክሮ እንደሚሰራ እንጂ ለተለየ ቡድን ጥቅም እንዳልቆመ ወይም ፈላጭ ቆራጭ እንዳልሆነ ያስመሰከረን መንግስት በተቻለ መጠን መደገፍ ይገባል።

“መንግስት” የሚል ርዕሰ ጉዳይ አለ። ትምህርት ቤቶች በዋነኝነት የሚያስተምሩት “የስነ ዜጋ” ትምህርትን ሲሆን ይህም በስልጣን ላይ ያለው መንግስት የተዋቀረበትን መንገድ

የሚጠቁም ብቻ ነው። “መንግስት” የሚለው ርዕሰ ጉዳይ ከስሩ የተለያዩ ርዕሶች ይኖሩታል፤ እነዚህም ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ ፍልስፍና፣ የፖለቲካ ስልጣን ወዘተ ... ናቸው። በአጠቃላይ “መንግስት” የሚለው ርዕሰ ጉዳይ እና እንዴት በትክክል ማስተዳደር ይቻላል የሚለው ነጥብ በጣም ጥልቅ ስለሚሆን ውስብስብ ሳይንስ ይሆናል ለማለት ይቻላል። የተሻለና ከሁከት የጸዳ መስተዳድር የሚፈልግ ካለ ትምህርቱ ለልጆች በለጋ እድሜአቸው ሊሰጥ እንደሚገባ ሐሳብ መስጠት ይኖርበታል። ስለ ርዕሰ ጉዳዩም ማንበብ ያስፈልጋል። ደግሞም ከባድ የሆኑትን ቃላት ፍች ከተረዳን አስቸጋሪ ርዕሰ ጉዳይም አይደለም።

ደግሞም ለአገሩ ሲል ላቡን የሚያንጠፈጥፈው፣ የሚዋጋውና ደሙን የሚያፈሰሰው ህዝብና የአስተሳሰቡ አራማጆች እንጂ መንግስት አይደለም። መንግስት መድማት ይቅርና ፈገግ እንኳ ማለት አይችልም። መንግስት ሐሳባዊ እንጂ ህያው የሆነ ነገር አይደለም። ህያው የሆነው እንደ ሉንታ ያለው ግለሰብ ነው።

ወደ ደሰታ የሚመራው ጎዳና በአምባገነን ጭቆና ጥላ ካጠላበት ጉዞው አሰቸጋሪ ይሆናል። ገራም የሆነና ለህዝቡ የቆመ መንግስት ጉዞውን ቀላል ያደርገዋል። እንዲህ ያለው መንግስት ድጋፍ ያሻዋል።

II. በጎ ፈቃድ[28] ያለውን ሰው አትጉዳ

ክፋ ሰዎች ሰው ሁሉ ክፋ ነው የሚል የጠበቀ አቋም ያላቸው ቢሆንም በዙሪያህ ብዙ ጥሩ ወንዶችና ሴቶች አሉ። አንተም አንዳንዶቹን ታውቅ ይሆናል።

እንደ እውነቱ ከሆነ ህብረተሰብ የሚንቀሳቀሰው በጎ ፈቃድ ባላቸው ወንዶችና ሴቶች ነው። የህዝብ ሰራተኞች፣ የአስተሳሰብ አራማጆች፣ በግሉ ዘርፍ ተሰማርተው ስራቸውን የሚያከናውኑ ሰዎች አብዛኞቹ በጎ ፈቃድ ያላቸው ናቸው። እንደዚያ ባይሆን ኖሮ ከረዥም ጊዜ በፊት ስራቸውን ባቆሙ ነበር።

እንዲህ ያሉት ሰዎች ለጥቃት የተጋለጡ ናቸው። መልካም ባህሪያቸው ስለ ራሳቸው ደህንነት ከልክ በላይ እንዳይጨነቁ ያግዳቸዋል። ሆኖም በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ የአብዛኞቹ ግለሰሞች ህልውና የተመካው በእነርሱ ላይ ነው።

ወንጀለኛው፣ የፕሮፓጋንዳ አቀንቃኙ[29] እና ስሜትን መኮርኮር የሚወደው የመገናኛ ብዙሃን በግለሰሞች በጎ ፈቃድ ባይሆን ኖሮ ህብረተሰብ ተግባሩን ሊያከናውን አይችልም ነበር ከሚለው መሰረታዊ የዕለት ተዕለት እውነታ የሰዎችን ትኩረት ለመስረቅ ይጥራሉ። የጎዳና ላይ ህግ አስከባሪ፣ የልጆች መካሪ፣ አረጋጊ እና አፅናኝ እነርሱ ስለሆኑ ይህ ዓለም እንዲቀጥልና ሰውም በምድር ላይ እንዲኖር ያደረጉት በጎ ፈቃድ ያላቸው ሰዎች መሆናቸው ቢዘነጋ አያስገርምም።

---

28. በጎ ፈቃድ፦ ለሌሎች የሚኖረን አመለካከት፣ ዝንባሌ፣ በተለምዶ በጎ ፈቃድ ያላቸው ሰዎች ማለት ለመሰል ሰዎች በጎ የሚያስቡና ሌሎችን ለመርዳት የሚጥሩ ሰዎች ማለት ነው።

29. የፕሮፓጋንዳ አቀንቃኝ፦ ፕሮፓጋንዳ መንዛቱን ሥራው ያደረገ ግለሰብ ወይም ቡድን ፕሮፓጋንዳ፦ የራስህን ሐሳብ ለማስፋፋት እና/ወይም ሌላውን ለመጉዳት ሲባል የሚሰራጭ ሐሳብ፣ መረጃ ወይም ወሬ፤ ብዙውን ጊዜ እውነት ስለመሆኑ ሳይታሰብበት የሚነገር፤ የሐሰት መረጃዎችን በሕትመት ውጤቶች፣ በቴሌቪዥን ወይም በሬድዮ በማውጣት አንድን ግለሰብ ጥፋተኛ ማድረግ፣ በሐሰት የአንድን ሰው ስም በማጥፋት ተደማጭነት አንዳያገኝ ማድረግ።

ሆኖም እነዚሁ ሰዎች ለጥቃት የተጋለጡ ስለሆኑ እነርሱን ለመከላከልና ከጉዳት ለመጠበቅ ጠንካራ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል። ምክንያቱም የአንተም ሆነ የቤተሰብህ ብሎም የወዳጆችህ ህልውና የተመካው በእነርሱ ላይ ነው።

ወደ ደሰታ የሚመራው ጎዳና ይበልጥ ቀላል የሚሆነው በጎ ፈቃድ ያላቸውን ሰዎች ስንደግፍ ነው።



12. አካባቢህን ጠብቅ[30] እንዲሁም አሻሽለው

12-1. ራስህን ጠብቅ።

አልፎ አልፎ አንዳንድ ሰዎች ራሳቸውን መለስ ብለው በማየት በመስታወት እያዩ ጊዜ ማጥፋት እንደሌለባቸው ስለሚሰማቸው በዙሪያቸው ያሉ ሰዎች እና የሚያዩት ትዕይንት አካል መሆናቸውን ይዘነጋሉ። ሌሎች ደግሞ በሰውነት አያያዛቸው ምክንያት በሌሎች እንደሚገመገሙ ይረሳሉ።

የልብስ ዋጋ ውድ ሊሆን ቢችልም ሳሙናንና ራስን በንጽህና ለመያዝ የሚያስችሉ ነገሮችን ማግኘት ብዙ አያስቸግርም። አንዳንድ ጊዜ ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉትን ዘዴዎች ማወቅ ሊያዳግት ቢችልም ቀስ በቀስ መማር ይቻላል።

በአንዳንድ ህብረተሰብ መካከል ስርዓት አጥቶ አልፎ ተርፎም በሰዎች ዘንድ አስቀያሚ ሆኖ መታየት እንደ ፋሽን ይቆጠር ይሆናል። በመሰረቱ ግን ይህ ለራስ አክብሮት ማጣትን የሚያመለክት ነው።

አንድ ሰው የሥራ እንቅስቃሴ በሚያደርግበት ወይም በሚሰራበት ወቅት አለባበሱ ያማረና የተስተካከለ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን ንፅህናውን ለመጠብቅ ይህ እንቅፋት ሊሆንበት አይችልም። ለምሳሌ ያህል አንዳንድ የአውሮፖና የአንግሊዝ ሰራተኞች ስራ ላይ እያሉም እንኳን ራሳቸውን ይጠብቃሉ። አንዳንድ የተሻሉ አትሌቶች በላብ ተጠምቀው እንኳን የሚያስከፋ ነገር እንደማይታይባቸው ማስተዋል ይቻላል።

ራሳቸውን በማይጠብቁ ሰዎች ውበቱን ያጣ አካባቢ በአንድ ሰው ሞራል[31] ላይ ድብታ የመጫን ስሙር ተፅእኖ ሊያስከትል ይችላል።

---

30. ጠብቅ፦ ከጉዳት መከላከል።
31. ሞራል፦ የአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን የአእምሮ ወይም የስሜት ዝንባሌ፤ የደህንነት ስሜት፣ በዚያው የመግፋት ፈቃደኝነት፤ የጋራ ዓላማ የመያዝ ስሜት።

ሰዎች ራሳቸውን ሲጠብቁ በማመስገን በማይጠብቁበት ጊዜ ደግሞ በደግነት ችግራቸውን እንዲያቃልሉ በመርዳት ጥሩ ሆነው እንዲታዩ አበረታታቸው። ይህ ሞራላቸውንና ለራሳቸው ያላቸውን ግምት ሊያሻሽል ይችላል።

12-2. አካባቢህን ተንከባከብ።

ሰዎች የራሳቸውን ንብረትና ይዞታ በማመሰቃቀል በተገቢው ሁኔታ የማይዙ ከሆነ ምስቅልቅሉ ለአንተም ይተርፋል።

ሰዎች የራሳቸውን ንብረትና ቤት መንከባከብ ስያቅታ ቸው አዚያ ቦታና ይዞታ ላይ መገኘት እንደማይገባቸዉ እና ንብረቱም የእኔ ንብረት አይደለም የሚል ስሜት እንዳላቸው የሚያመላክት ነው። በልጅነታቸው "የተሰጧቸው" ነገሮች በብዙ ማሳሰበያ የታጀቡ ሆነው ወይም ደግሞ እነዚህን ነገሮች በወንድሞቻቸው፣ በእህቶቻቸው ወይም በወላጆቻቸው ተነጥቀው የነበር ሊሆንና ይህም መጥፎ ስሜት አሳድሮባቸው ሊሆን ይችላል።

እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ይዞታቸውን፣ ክፍላቸውን፣ የስራ ቦታቸውንና ተሽከርካሪያቸውን የሚይዙበት መንገድ ንብረቱ ባለቤት እንደሌለው ይመስክራል። ከዚህ የከፋው ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ባለቤትነትን በመቃወም የሚንፀባረቅ ቁጣ መኖሩ ነው። ስርዓት አልበኝነት[32] የዚህ መገለጫ ነው። "ያ ባለቤት የሌለዉ" ተሽከርካሪ ወይም ቤት ብዙ ሳይቆይ ጨርሶ ባክኖ ይቀራል።

በዝቅተኛ ገቢ የሚሰሩ ቤቶችን ለመገንባትና ለመያዝ የሚጥሩ ሰዎች ውድመቱ የሚሰፋፋበት ፍጥነት ተሰፋ ያስቆርጣቸዋል። በአጠቃላይ ሲታይ ድሆች ብዙ ንብረት አይኖራቸውም ወይም ደግሞ ከነጭራሹ ምንም ንብረት የላቸውም። በብዙ መንገድ ስለሚገፋም የማንም ወገን እንደሆኑ አይሰማቸውም።

ይሁን እንጂ ድሆችም ሆኑ ሃብታሞች በማናቸውም ምክንያት ንብረታቸውንና የሚኖሩበትን ቦታ የማይንከባከቡ ከሆነ

32. ሥርዓት አልበኝነት፡ የሕዝብና የመንግሥት ንብረትን በተለይም ውብ የሆኑትንና የጥበብ ሥራዎችን በጥላቻ ስሜት ተነሳስቶ ሆን ብሎ ማውደም።

አካባቢያቸው እንዲዝረከረክ ምክንያት ይሆናሉ። አንተም እንዲህ ያሉ አጋጣሚዎችን ማሰብ እንደምትችል እርግጠና ነኝ።

እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች በህይወታቸው አለኝ የሚሉት ንብረት ይኖር እንደሆነ ወይም ራሳቸውን የሚኖሩበት ማህበረሰብ ክፍል አድርገው የሚቆጥሩበት ቦታ እንዳላቸው ብትጠይቃቸው አስገራሚ መልስ ታገኛለህ። ቢሆንም እርዳቸው።

ንብረትንና ይዞታን የማደራጀት ክህሎት በትምህርት ሊገኝ ይችላል። አንድ ዕቃ ሌላ ጊዜ ተፈልጎ እንዲገኝ ከተነሳበት ቦታ ላይ ተመልሶ ሊቀመጥ ይገባል የሚለው ሃሳብ ለአንድ ሰው አዲስ ግንዛቤ ሊሆን ይችላል። አንዳንዶች ካላቸው ጊዜ ውስጥ ከፊሉን የሚያጠፋት እቃ በመፈለግ ነው። ለማደራጀት የምንመድበው የተወሰነ ጊዜ በኋላ ስራውን ለማፋጠን ስለሚረዳ መልሶ የሚክስ ነው። ይህ አንዳንዶች እንደምያስቡት ጊዜ ማባከን አይደለም።

የራስህን ንብረትና ይዞታ ከጉዳት ለመጠበቅ ሌሎች የራሳቸውን ንብረትና ይዞታ እንዲጠብቁ አድርግ።

12-3. ፕላኔቷን ምድራችንን በመንከባከብ ረገድ የበኩልህን አገዛ አድርግ።

አንድ ሰው በፕላኔቷ ላይ የራሱ ድርሻ አለው የሚለውና ፕላኔቷን ለመንከባከብ የሚደረገውን ጥረት ሊደግፍ ይችላል ደግሞም ይገባል የሚለው ሐሳብ ለአንዳንዶች በጣም የተጋነነና ከእውነታው የራቀ እንደሆነ ይሰማቸዋል። ይሁን እንጂ ዛሬ በሌላኛው የዓለም ክፍል የሚከናወነው ነገር የቱንም ያህል ርቆ የሚፈፀም ቢሆን በቤትህ ያለውን ሁኔታ የሚነካ ሊሆን ይችላል።

በቅርቡ በቬነስ ላይ የተደረገው የህዋ ጥናት እንዳረጋገጠው የእኛም ዓለም ህይወትን ማኖር የማትችልበት ደረጃ ላይ ልትደርስ ትችላለች። ይህ ደግሞ በእኛም የህይወት ዘመን ሊከሰት ይችላል።

ብዙ ደኖች ከተጨፈጨፉ፣ ብዙ ወንዞችና ባህሮች ከተበከሉ አንዲሁም ከባቢውን አየር ከመረዝነው የእጃችንን አናገኛለን። የምድር የሙቀት መጠን እንደ ብረት ምጣድ የሚፋጅ ይሆናል፤ ዝናቡ አሲዳማ (ሰልፈሪክ አሲድ) ሊሆን ይችላል።

ህይወት ያለው ነገር ሁሉ ጨርሶ ሊጠፋም ይችላል።

አሁን አንድ ሰው "ይህ ሁሉ ነገር እውነት ቢሆን እንኳ እኔ ምን ማድረግ እችላለሁ?" ብሎ ሊጠይቅ ይችላል። ሌሎች ሰዎች ምድርን ሲያመሰቃቅሉ የሚጨነቅና የሚጠበብ ሰው ካለ አንድ ነገር አድርጓል ማለት ነው። ምድርን ማበላሸት ተገቢ አይደለም የሚል አቋም ያለውና ይህንን አመለካከቱን ለሌሎች የሚገልፅም እንኳ ቢሆን አንድ ነገር አድርጓል።

ፕላኔታችንን መንከባከብ የሚጀምረው ጓሮአችንን በመንከባከብ ነው። ከዚያም ወደ ትምህርት ቤት ወይም ወደ ስራ የምንሄድበትን አካባቢ በመንከባከብ ይቀጥላል። ከዚያም አልፎ ለሽርሽር ወይም ለእረፍት የምንሄድባቸውን ቦታዎች መንከባከብን ይጨምራል። ሽንተረሩን እና የውሃ ምንጮችን የሚያቆሽሹውን ቆሻሻ፣ እሳት የሚያስነሳውን የደረቀ ቁጥቋጦ የሚያባብስ ነገር ማድረግ የለብንም። እንዲያውም በአንፃሩ ጊዜ ሲኖረን ይህንን ለማሻሻል መጣር ይኖርብናል። ዛፍ መትከል ትንሽ ነገር ሊመስል ቢችልም በራሱ አንድ እርምጃ ነው።

በአንዳንድ አገሮች በእድሜ የገፋና ስራ አጥ የሆኑ ሰዎች ስራ ፈተው አይቀመጡም። ከዚህ ይልቅ የአትክልት ስፍራዎችን፣ መናፈሻዎችንና ደኖችን እንዲንከባከቡ፣ ቆሻሻ እንዲያፀዱና ምድራችንን እንዲያስውቡ ይደረጋል። ምድራችንን ለመንከባከብ የሚጎድለን ጥሪት የለም። ችግሩ ቸልተኝነት ነው። ለምሳሌ ያህል በ1930 በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የተቋቋመው የሲቪል ዜጎች የተፈጥሮ ጥበቃ ጓድ ስራ አጥ የሆኑ ሰዎችንና ወጣቶችን ሃይል ያስተባበረ ሲሆን በዚያ የጨለማ ድባብ በዋጠው ዘመን ወጪ ከተደረገበት በላይ ለግዛቲቱ ከፍተኛ ሃብት ያስገኘ ብቸኛ ድርጅት ነው ማለት ይቻላል። ሰፊ አካባቢ የሚሸፍን ደን በመትከል በዩናይትድ ስቴትስ አካባቢ በሚገኘው የፕላኔቷን ክፍል

ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ተግባር አከናውኗል። አሁን የሲቪል ዜጎች የተፈጥሮ ጥበቃ ጓድ በስራ ላይ አይደለም። እንደነዚህ ዓይነት ፕሮጀክቶች ጠቃሚ እንደሆኑ መናገርን የመሳሰሉ ቀላል አገዛዎችን ማድረግ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ ስራ የሚሰሩ ድርጅቶችንና ይህንን ሃሳብ የሚያራምዱ ወገኖችን መደገፍ ይቻላል።

የቴክኖሎጂ እጥረት የለብንም። ሆኖም ቴክኖሎጂም ሆነ ቴክኖሎጂን በስራ ላይ ማዋል ወጪ ይጠይቃል። የታሰበባቸውና ሰውን ሁሉ በጅምላ የማይደቁሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ሥራ ላይ በሚውሉበት ጊዜ ገንዘብ ይገኛል። ደግሞም እንዲህ አይነት ፖሊሲዎች አሉ።

ሰዎች ምድራችንን ለመንከባከብ ሊያደርጓቸው የሚችሏቸው ብዙ ነገሮች አሉ። አንድ ሰው የሚወስደው የመጀመሪያው እርምጃ ማድረግ ያለበትን ነገር ማሰብ ነው። ከዚያም ሌሎችም ማድረግ እንዳለባቸው በመንገር ይቀጥላል።

የሰው ልጅ ምድርን የሚያጠፋበት አቅም ደረጃ ላይ ደርሷል። ምድራችንን ከጥፋት የሚታደግበትን ብቃት እንዲያዳብርና ለዚሁ የሚበጅ እርምጃ እንዲወስድ ሊገፋፋ ይገባል። ከሁሉም በላይ ግን ደግሞ የቆምንበት ምድር ነውና።

ሌሎች ሰዎች አካባቢያቸውን ለመጠበቅና ለማሻሻል ምንም እርዳታ የማያበረክቱ ከሆነ ወደ ደሰታ በሚመራው ጎዳናም ወደፊት መጓዝ አይቻልም።

13. አትሰረቅ

አንድ ሰው ለንብረት ባለቤትነት አክብሮት ከሌለው የራሱም ንብረትና ይዞታ አደጋ ላይ ይወድቃል።

አንድ ሰው በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ በሃቀኝነት ንብረት ማከማቸት ካልቻለ ማንኛውም ሰው በምንም መንገድ የራሱ የሆነ ነገር ሊኖረው አይችልም የሚል አቋም ያለው ያስመስልበታል። ሆኖም ከእርሱም ቢሆን ለመሰረቅ አትሞክር!

አንድ ሌባ በአካባቢው ግራ መጋባትን ይፈጥራል። ይሄ ነገር የት ደረሰ? ያኛው ነገር የት ሄደ? የሚል ሁኔታ ይፈጥራል። ሌባ የሚፈጥረው ችግር ከተሰረቀው እቃ ዋጋ በላይ ነው።

ተፈላጊ የሚባሉ እቃዎችን በማስታወቂያ በማየት፣ የንብረት ባለቤት ለመሆን የሚያበቃ ስራ ለመስራት ካለመቻል ወይም አንዲሁ በውስጣዊ ግፊት በመነዳት የሚሰርቁ ሰዎች በጣም ብዙ ዋጋ የሚያወጣን ነገር በትንሽ ዋጋ አንዳገኙት ይሰማቸው ይሆናል። ሆኖም ችግሩ ያለው እዚህ ላይ ነው። ሌባው የሚከፍለው ዋጋ ልንገምተው ከምንችለው በላይ ነው። በታሪክ የሚታወቁ ከባድ ዘራፊዎች "የህይወትን ጣዕም" ሊያጣጥሙ በማይችሉበት ሁኔታ ጭው ያለ ዋሻ ወይም እስር ቤት ውስጥ ህይወታቸውን ለማሳለፍ ተገድደዋል። የትኛውም ከፍተኛ ዋጋ ያለው የተሰረቀ ንብረት ከዚህ አስከፊ እጣ ጋር አይመጣጠንም።

የተሰረቁ ንብረቶች ዋጋ በእጅጉ ይቀንሳል። ሁልጊዜ መደበቅ አለባቸው። ነፃነትን ያሳጣሉ። በኮሙኒስት ግዛቶች ሳይቀር አንድ ሌባ እስር ቤት አንዲገባ ይደረጋል።

መስረቅ አንድ ሰው አንድን ነገር በሀቅ ሰርቶ ሊያገኝ እንደማይችል አምኖ መቀበሉን የሚያሳይ ነው። ወይም ደግሞ

ነካ ያደርገዋል ማለት ነው። አንድ ሌባ ብትጠይቁት መልሱ ከሁለቱ አይወጣም።

ወደ ደስታ በሚመራው ጎዳና ላይ ከተሰረቁ
ንብረቶች ጋር መንዝ አይቻልም።



14. እምነት የሚጣልብህ ሁን

አንድ ሰው በዙሪያው ባሉት ሰዎች ላይ እምነት መጣል ካልቻለ ህይወቱ አደጋ ላይ ይወድቃል። የተማመነባቸው ሰዎች አንደጠበቃቸው ሆነው ካልተገኙ የአርሱም ህይወት ሊመሰቃቀልና ህልውናው ጭምር አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል።

የጋራ መተማመን በሰዎች መካከል ባለ ግንኙነት ትልቅ የማዕዘን ድንጋይ ነው። የጋራ መተማመን ከሌለ ጠቅላላው መዋቅር ሊፈርስ ይችላል።

ታማኝነት ከፍተኛ ዋጋ ያለው ባህርይ ነው። አንድ ሰው ይህንን ባህርይ ካዳበረ ከፍ ያለ ዋጋ ይኖረዋል። ከሌለው ደግሞ ዋጋ ቢስ ይሆናል።

በዙሪያው ያሉትን ሰዎች ተመሳሳይ ባህርይ እንዲያዳብሩና አንዲያሳዩ ሊያበረታታቸው ይገባል። አነርሱም ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች ሰዎች የሚጠቅሙ ይሆናሉ።

14-1. ቃልህን ጠብቅ።

አንድ ሰው ተስፋ ከሰጠ ወይም ቃል ከገባ ወይም አንድ ነገር አደርጋለሁ ካለ ቃሉን መጠበቅ ይኖርበታል። አንድ ነገር አደርጋለሁ ካለ ማድረግ አለበት። አንድ ነገር አላደርግም ካለ ደግሞ ማድረግ የለበትም።

ለሌላው ሰው የሚኖረን አክብሮት በአጅጉ የሚመካው ግለሰቡ ቃሉን ይጠብቃል ወይስ አይጠብቅም በሚለው ላይ ነው። ለምሳሌ ያህል፣ ወላጆች አንኳ የገቡትን ቃል ሳይጠብቁ ከቀሩ ልጆቻቸው ለአነርሱ ያላቸው ግምት በአጅጉ ሲቀንስ ሊያስተውሉ ይችላሉ።

ቃላቸውን የሚጠብቁ ሰዎች አምነት ይጣልባቸዋል። አንዲሁም ይደነቃሉ። ቃላቸውን የማይጠብቁ ሰዎች ግን ይናቃሉ። ብዙውን ጊዜ ቃላቸውን የሚያጥፉ ሰዎች ጨርሶ ሁለተኛ እድል አንኳን አያገኙም።

ቃሉን የማይጠብቅ ሰው በተለያዩ አይነት “ዋስትናዎች” እና “ገደቦች” ስለሚታጠር ከሌሎች ጋር ያለው ጤናማ ግንኙነት እንኳን ሳይቀር ይገደብበታል። የገቡትን ቃል ሳይጠብቁ ከመቅረት የከፋ ከባልንጀሮች የሚያለያይ ግዞት የለም።

አንድ ሰው እንደዋዛ ተስፋ እንዲሰጥ መፍቀድ አይኖርብህም። ተስፋ ከሰጠ መፈፀም እንዳለበት ሊወተወት ይገባል። የገቡትን ቃል ከማይፈፅሙ ሰዎች ጋር መተባበር ህይወትን ሊያመሰቃቅል ይችላል። ይህ ቀላል ጉዳይ አይደለም።

ወደ ደስታ በሚመራው ጎዳና ላይ የሚደረገው ጉዞ እምነት ከሚጣልባቸው ሰዎች ጋር ሲሆን በጣም ይቀላል።





15. ግዴታዎችህን[33] ተወጣ።

በህይወት ጎዳና ላይ ግዴታዎች መኖራቸው አይቀርም። እንደ እውነቱ ከሆነ አንድ ሰው የሚወለደው ከተወሰኑ ግዴታዎች ጋር ሆኖ ከዚያ በኋላ ግዴታው እየጨመረ ይሄዳል። አንድ ሰው ወላጆቹ ወደዚህ ዓለም ስላመጡትና ስላሳደጉት የእነርሱ ባለ እዳ ነው የሚለው ሃሳብ አዲስ ነገር አይደለም። ይህ ለወላጆች አንደ ውለታ የሚታሰብላቸው ነገር ነው። የሆነ ሆኖ ግዴታም ነው። ይህንን ሕግንም ሳይቀር የሚገነዘበው ነገር ነው። አንድ ሰው እድሜው እየጨመረ ሲሄድ በሌሎች ዘንድ ማለትም በጓደኞቹ፣ በማህበረሰቡ አልፎ ተርፎም በዓለም ደረጃ ጭምር ያለበት ግዴታም እየጨመረ ይሄዳል።

ለአንድ ሰው "ግዴታውን አለመወጣት" ና ላለመርካት አለመፍቀድ ትልቅ ጉዳት ነው። ማንኛውም ትንሽ "የልጅነት ዓመፅ" ሌሎች ህጻን ወይም ልጅ ግዴታውን ለመወጣት "ያሉትን ሳንቲሞች" ለመቀበል እምቢ በማለታቸው የተፈጠረ አይደለም። ፈገግታ የልጅ ለእርዳታ መፍጨርጨር ሊሆን የሚችለው የወጣት ወይም የመልካም ሴት ልጅ ምክር ተቀባይነት ሳያገኝ ይቀራል። በመጥፎ ሁኔታ የተነጣጠሩ ወይም ዘወትር በመጥፎ ሁኔታ የታቀዱ ሊሆኑ ይችላሉ። በፍጥነትም ይደበዝዛሉ። እንደዚህ ዓይነት ጥረቶች ያለውን መዓት ዕዳ ሳይከፍሉ ሲቀሩ በሌላ ሰበብ ይተካሉ። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል "አንድ ሰው በእርግጥ ምንም ዕዳ የለበትም"፣ "ድሮ ግዴታ ነበረብኝ"፣ "ልወለድ ብዬ አልጠየቅሁም"፣ "ወላጆቼ ወይም አሳዳጊዎቼ መልካም አይደሉም" "መኖር ምንም አይጠቅምም" የሚሉትን የመሳሰሉ ይሆናሉ። ሆኖም ግን ግዴታዎቹ እየተከመሩ ይሄዳሉ።

33. ግዴታ፡ በውለታ ወይም በተለየ አገልግሎት ምክንያት ለሌላው ሰው ባለ ዕዳ መሆን፤ አንድ ግለሰብ ከሆነ ነገር እንዲታቀብ ወይም የሆነ ነገር እንዲያደርግ የሚጣልበት ግዴታ፣ የሚያስገድደው ውል፤ ወይም ሌላ ዓይነት ማኅበራዊ ወይም የሞራል ግዴታ።

አንድ ሰው ግዴታውን የሚወጣበትን መንገድ ካላስተዋለ “ጫናው” ከባድ ሊሆን ይችላል። የተለያየ ዓይነት ግላዊ ወይም ማህበራዊ ቀውስ ሊያስከትል ይችላል። ብዙውን ጊዜ መፈጸም ያለባቸው ግዴታዎች ሳይፈፀሙ ከቀሩ ባለውለታ የሆኑት ወገኖች የማይፈልጉት ዓይነት ምላሽ ያጋጥማቸዋል።

ያልተወጣቸው የሞራልና ማህበራዊ ግዴታዎች እንዲሁም ያልተወራረዱ የገንዘብ እዳዎች ያሉበትን ሰው ለመርዳት ከግለሰቡ ጋር ሆኖ ያሉበትን ግዴታዎች በሙሉ በመዘርዘር እነዚህን ግዴታዎች *በሙሉ* መወጣት የሚችልበትን መንገድ መቀየስ ይቻላል።

አንድ ልጅም ሆነ አዋቂ አለብኝ ብለው የሚያስቡትን ከገንዘብ ጋር ያልተያያዘ ግዴታ ለመወጣት የሚያደርጉትን ጥረት አምኖ መቀበል ያስፈልጋል። የገንዘብ ግዴታዎችን መወጣት ስለሚቻልበት መንገድ የጋራ መፍትሄ ለማምጣት እገዛ ማድረግ ይገባል።

አንድ ሰው ሊወጣው የማይችለው ግዴታ ወይም ሊከፍለው የማይችለው ዕዳ ውስጥ እንዳይገባ ተከላከል።

አንድ ሰው ያልተወጣቸው ግዴታዎችና ያልከፈላቸው እዳዎች ካሉበት ወደ ደስታ በሚመራው ጎዳና ላይ የሚያደርገው ጉዞ አስቸጋሪ ነው።

16. ትጉ ሁን

ሥራ ሁሉ ሁልጊዜ አስደሳች አይደለም።

ነገር ግን ዓላማ የሌለውን ሥራ ፈትና የተሰላቸ ሕይወት ከሚኖሩ ሰዎች ይልቅ ደስታ የሌላቸው ጥቂቶች ናቸው። ልጆች የሚሠሩት ሥራ በማይኖራቸው ወቅት ለእናታቸው ድብርት ይሆናሉ። በተለምዶ "በመንግሥት አርዳታ" ወይም ከመንግሥት "የሥራ አጥ ደሞዝ" የሚከፈል ቢሆን እንኳን የሥራ አጥነት የዝቅተኝነት ስሜት ይሰማቸዋል። ምንም የሚያከናውነው ሥራ የሌለው ጡረታ የወጣ ሰው ካለመሥራቱ የተነሳ እንደሚሞት መረጃዎች ያመለክታሉ።

ለመዝናኛ በጉዞ ወኪሎች ጥሪ ተቃልሎ የሚሄድ ጎብኚ እንኳ ለአስጎብኚዎቹ የሚሠራላቸው ሥራ ከሌለ ይደብራቸዋል።

በስራ በመጠመድ ብቻ ሃዘንን መቀነስ ይቻላል።

አንድን ነገር ማከናወን መቻል ሞራልን በእጅጉ ይገነባል። አንዲያውም ውጤት የሞራል መሰረት ነው ተብሎም ሊገለፅ ይችላል።

ትጉ ያልሆኑ ሰዎች የስራ ጫናውን በዙሪያቸው ባሉ ሰዎች ላይ ያራግፋሉ። ሸክሙን በሌላው ሰው ጫንቃ ላይ የመጣል ዝንባሌ ይኖራቸዋል።

ስራ ፈት ከሆኑ ሰዎች ጋር ተስማምቶ መዝለቅ ያስቸግራል። ድብታ እንዲጫጫነን ከማድረጋቸውም በላይ አደገኛ ሊሆኑም ይችላሉ።

ለዚህ መፍትሄ የሚሆነው እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች የሆነ ነገር እንዲሰሩ ማሳመንና በስራው እንዲጠመዱ ማድረግ ነው። ወደ ውጤት ከሚያደርስ ስራ ዘላቂ የሆነ ጥቅም ይገኛል።

ወደ ደስታ የሚመራው ጎዳና ወደ
ተጨባጭ ውጤት የሚመራንን የስራ ትጋት
የሚጨምር የላቀ ጎዳና ነው።

17. ብቁ[34] ሁን

በጣም ውስብስብ መሳሪያዎች፣ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑ ማሽኖችና ተሽከርካሪዎች ባሉበት ዘመን የአንድ ሰው ህልውናም ሆነ የቤተሰቡና የወዳጆቹ ህልውና በእጅጉ የተመካው በሌሎች አጠቃላይ ብቃት ላይ ነው።

በገበያ ቦታ፣ በሳይንስ፣ በሰብዓዊነት ተግባርና በመንግስታት ዘንድ ብቃት የለሽ[35] መሆን የጥቂቶችንም ሆነ የብዙዎችን ህይወትና የወደፊት እጣ ፈንታ አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል።

እንደዚህ ዓይነት ብዙ ምሳሌዎችን ማሰብ እንደምትችል አርግጠኛ ነኝ።

የሰው ልጅ ሁል ጊዜ እጣ ፈንታውን ለመወሰን ሲሞክር ኖሯል። አጉል እምነት፣ ትክክለኛውን አማልክት መለማመን፤ ከታደነው እንስሳ ዙሪያ መደነስና የመሳሰሉት ሁሉ የቱንም ያህል ውጤት አልባ ቢመስሉ እጣ ፈንታን ለመወሰን የሚደረጉ ጥረቶች ተደርገዉ ሊታዩ ይችላሉ።

የሰው ልጅ ማሰብን፣ ለእውቀት ቦታ መስጠትንና እነዚህን ከክህሎት ጋር አዳምሮ ስራ ላይ ማዋልን አስከተማረበት ጊዜ ድረስ አካባቢውን መግዛት አልቻለም። እውነተኛው "የሰማይ ስጦታ" ብቁ የመሆን ችሎታ ሳይሆን አይቀርም።

መሰረታዊ በሆኑ ግብና ተግባራት ረገድ የሰው ልጅ ለክህሎትና ለችሎታ ከፍ ያለ ቦታ ይሰጣል። አንድ ጀግና ወይም አትሌት እነዚህን ባህርያት ሲያሳይ ደግሞ ለግለሰቡ የአምልኮ አከል ክብር ይሰጠዋል።

---

34. ብቃት፦ ሥራን በሚገባ ማከናወን መቻል፤ ሥራን በጥሩ ችሎታና በክህሎት ማከናወን፤ የሚፈለገውን ብቃት አሟልቶ መገኘት።
35. ብቃት የለሽ፦ ተፈላጊውን እውቀት ወይም ክህሎት ወይም ችሎታ ማጣት፤ ከባድ ስህተቶችን መፈጸም።

የእውነተኛ ብቁነት መለኪያው የመጨረሻው ውጤት ነው።

አንድ ሰው ብቁ ሆኖ በተገኘ መጠን የዚያኑ ያህል ህልውናውን ማስጠበቅ ይችላል። ብቁ ሆኖ ባልተገኘ መጠን ደግሞ የዚያኑ ያህል ህልውናው ይከስማል።

በማንኛውም ጠቃሚ ግብ ረገድ ብቃትን እንዲያዳብሩ ሌሎችን አበረታታ። ይህንን ያደረገ ስታገኝ ደግሞ አመስግነው እንዲሁም ሽልመው።

ከፍ ያሉ የብቃት ደረጃ የምትሻ ሁን። የማህበራዊ ኑሮ ጣእም መለክያዉ አንተ፣ ቤተሰብህና ወዳጆችህ በህብረተሰቡ ውስጥ አስተማማኝ በሆነ መንገድ መኖር ትችላላችሁ ወይ የሚል ነው።

ማስተዋል፣ ጥናትና ተግባራዊ ልምምድ[36] የብቃት መሰረት ነው።

፲፯-፩. አስተውል።

አንተ ራስህ የምታየውን እይ እንጂ ሌላው ሰው እንድታይ የሚያደርግህን መሆን አይኖርበትም።

አንተ ያስተዋልከው ሰንተ ያስተዋልከው ነው። ነገሮችን ወይም ህይወትንና ሌሎች ሰዎችን የምታየው በቀጥታ እንጂ በስሜታዊነት ደመና፣ በፍርሃት መጋረጃ ወይም በሌሎች ሰዎች ትንታኔ ተጋርደህ መሆን የለበትም።

ከሌሎች ጋር ከመከራከር ይልቅ ቆም ብለው እንዲያስ ተውሉ አድርግ። አንድ ሰው በጥሞና አንዲያሰተውል አጥብቆ በማሳሰብ ብቻ ስውር የሆነው ውሸት ይፋ ሊወጣ፣ የተሰወረው ሊጋለጥ፣ ውስብስብ የሆነው እንቆቅልሽ ሊፈታና ድብቅ የሆነው ራእይ ሊገለጥ ይችላል።

ሌላው ሰው ነገሮች በጣም አስቸጋሪና ግራ የሚያጋቡ ሆነውበት ሃሳቡ ሲባዝን ከተመለከትክ ቆም ብሎ እንዲያስተውል አድርግ።

---

36. ልምምድ፦ ክህሎትን ለማዳበር ወይም ለማሻሻል አንድን ተግባር ደግሞ ደጋግሞ ማከናወን።

ብዙውን ጊዜ አንድን ነገር ካስተዋሉት ግልፅ አንደሚሆንላቸው ይገነዘባሉ። ከዚያም አንዳንድ ጉዳዬችን አንዴት መከወን አንዳለባቸዉ ይገነዘባሉ። ሆኖም ለአነርሱ ለራሳቸው ግልጽ ካልሆነላቸው አንደ አነርሱ ሆነህ አስተውልላቸው። ነገር ግን ይህም ቢሆን ላያሳምናቸው ይችላል። በዓለም ላይ ያለ መመሪያ፣ ትእዛዝና ቅጣት ሁሉ አንድ ላይ ቢሰባሰብ ግራ መጋባታቸውን ሊያስወግድ አይችልም።

የሚያስተውሉበትን አቅጣጫ መጠቆምና አንዲያስተውሉ ሐሳብ መስጠት ቢቻልም የመጨረሻው መደምደሚያ ግን የአነርሱ ነው።

አንድ ህፃን ወይም ጎልማሳ የሚመለከተው ራሱ የሚያየውን ሲሆን ይህ የተመለከተው ነገር ደግሞ ለእርሱ እውነታ ነው።

እውነተኛ ብቃት አንድ ሰው ነገሮችን ለማስተዋል ባለው ችሎታ ላይ የተመሰረተ ነው። አንድ ሰው የተካነና እርግጠኛ ሊሆን የሚችለው ይህንን እውነታ ካስተዋለ ብቻ ነው።

17-2. ትምርት

ሌላ ሰው ስለ አንተ የተሳሳተ መረጃ ደርሶት የሚያውቅበት ጊዜ አለ? ከሆነስ ይህ በአንተ ላይ ያስከተለው ችግር ነበር?

ይህ የተሳሳተ መረጃ ምን ያህል ቀውስ ሊያስከትል አንደሚችል ፍንጭ ሊሰጥህ ይችላል። አንተም ብትሆን ስለ ሌላ ሰው አንድ የተሳሳተ መረጃ ሊኖርህ ይችላል።

እውነቱን ከሐሰቱ መለየት ግንዛቤን ያጠራል።

በዙሪያችን ብዙ የተሳሳተ መረጃ አለ። እኩይ አላማ ያላቸው ግለሰቦች የራሳቸውን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ ፈጥረው ያወራሉ። አንዳንድ ጊዜ ይህ የሚመነጨው አንዲሁ እውነታውን ካለማወቅ ሲሆን ይህ ደግሞ እውነተኛው መረጃ ተቀባይነት አንዳያገኝ ያግዳል።

አብይ የሆነው የመማር ሂደት ያሉ መረጃዎችን መመርመርን፣ እውነተኛውን ከሐሰተኛው አንዲሁም

የሚያስፈልገውን ከማያስፈልገው መለየትንና አንድ ሊሰራበት የሚችል መደምደሚያ ላይ መድረስን ይጠይቃል። አንድ ሰው ይህንን ካደረገ ብቃትን ለማግኘት በሚያስችለው ጎዳና ላይ እየተጓዘ ነው ማለት ነው።

ማንኛውም "እውነት" እውነትነቱ የሚለካው *ለአንተ* እውነት ከሆነ ብቻ ነው። አንድ መረጃ ስታገኝ ሙሉ በሙሉ ያልተረዳሃቸውን ቃላት ከተረዳህ በኋላም አጠቃላዩን ይዞታ ስትመለከተው እውነት የማይመስል ከሆነ በአንተ ሚዛን እውነት አይደለም ማለት ነው። አትቀበለው። ከፈለግህ ተጨማሪ ምርምር አድርግና *ለአንተ* እውነት የሆነ መደምደሚያ ላይ ድረስ። ደግሞም ባገኘኸው እውነት የምትጠቀመው ወይም የማትጠቀመው፣ የምታስበው ወይም የማታስበው *አንተው* ነህ። አንድ ሰው ሌላው ሰው ስለነገረው ብቻ አይኑን ጨፍኖ "እውነቶች" ወይም "እውነታዎች" የሚባሉትን፣ ለአርሱ ግን እውነት የማይመስሉትን ብሎም ውሸት የሆኑትን "እውነቶች" ወይም "እውነታዎች" ከተቀበለ መጨረሻው ውጤት የማያስደስት ይሆናል። ይህም ብቁ ካለመሆን ጋር የሚመደብ ነው።

ሌላው መማር የምንችልበት መንገድ ደግሞ ነገሮችን በአእምሮ የማስታወሻ ማህደር መመዝገብ ነው። እነዚህም የቃላትን ፊደላት፣ የሒሳብ ሰንጠረዦችንና ቀመሮችን እንዲሁም ከየትኛው ቀጥሎ የትኛውን እጨናለሁ የሚሉትን የመሳሰሉ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁንና ቀላል ነገሮችን በአእምሮ በመያዝ ረገድም ቢሆን አንድ ሰው የሚያጠናው ነገር ለምን እንደሚጠቅም ብሎም እንዴትና መቼ እንደሚጠቀምበት ማወቅ ይኖርበታል።

መማር በመረጃ ላይ መረጃ መቆለል ማለት ብቻ አይደለም። አዳዲስ ግንዛቤዎችንና ነገሮችን በተሻለ መንገድ ለማከናወን የሚያስችሉ መንገዶችን ማግኘት ነው።

በህይወታቸው የሚሳካላቸው ሰዎች ማጥናትና መማራቸውን የማያቆሙ ሰዎች ናቸው። ብቃት ያለው መሃንዲስ አዳዲስ

ዘዴዎችን ለማግኘት ይጥራል፤ አንድ ጥሩ አትሌት ውጤቱን በየጊዜው ይገመግማል፤ አንዲሁም ማንኛውም ባለሙያ ዕሁፎቹን አንድ ላይ አስቀምጠ ባስፈለገው ጊዜ ይመረምራቸዋል።

አዲስ ሞዴል የእንቁላል መምቻ ወይም እቃ ማጠቢያ ማሽን፣ አዲስ ሞዴል መኪና፣ ሁሉም በብቃት ስራ ላይ ከመዋላቸው በፊት እቃዎቹን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል የተወሰነ ጥናት ሊደረግባቸውና እውቀት ያስፈልጋል። ሰዎች መማርን ችላ ሲሉ ብዙውን ጊዜ በማእድ ቤት ውስጥም አደጋ ይደርሳል። በአውራ ጎዳናዎችም ላይ ብዙ ደም ይፈስሳል።

ከእንግዲህ በሕይወቱ ምንም የምማረው ነገር አይኖርም ብሎ የሚያስብ ሰው በጣም አብሪተኛ ነው። አይኑን በጋረደው የስሜታዊነት ደመና ላይና በያዘው የሐሰት መረጃ ላይ የእውነት ብርሃን ፈንጥቆ የራሱንና የሌሎችን ሰዎች ህይወት ለማገዝ የማይፈቅድ ሰው በአደገኛ ሁኔታ የታወረ ነው።

አንድ ሰው መማርና የተማረውን በስራ ላይ ማዋል እንዲችል የሚረዱ የአጠናን ዘዴዎች አሉ። በአጭር አነጋገር ትምህርት የሚናገሩትን የሚያውቁና ግልፅ ያልሆኑ ነገሮችን ሊያብራሩ የሚችሉ፣ ሌሎች የማመሳከሪያ ዕሁፎችን እና/ወይም ሌሎች ለርዕሰ ጉዳዩ ተስማሚ የሆኑ ክንውኖችን የሚዳስሱ፣ አንድ ሰው ያለውን የተሳሳተ መረጃ የሚለዩና አሁን ለአንተ እውነት የሆነውን ነገር መሰረተ በማድረግ ሀሰት የሆነውን ከእውነቱ መለየት የሚችሉ አስተማሪዎች እና/ወይም ጽሁፎችን ማግኘትን ይጨምራል። የመጨረሻው ውጤት እርግጠኝነትና ብቃት ይሆናል። ይህ ደግሞ በጣም ብሩህና መልሶ የሚክስ የሕይወት ተሞክሮ ነው። አስቸጋሪ የሆነን ተራራ በምርኩዝ ወጥተው ጫፍ ላይ ሲደርሱ ጠቅላላውን ዓለም በአዲስ ዓይን እንደሚያዩ ያህል ነው።

አንድ ስልጣኔ ህልውናውን ለመጠበቅ በትምህርት ቤቶች የማጥናትን ልማድና ችሎታ መኮትኮት አለበት። ትምህርት ቤት ልጆች ቤት እንዳይውሉ ሲባል ብቻ የሚላኩበት ቦታ

አይደለም። ለዚህ ብሎ ልጅን ትምህርት ቤት መላክ ከወጪው ጋር አይመጣጠንም። ትምህርት ቤት ልጆች እንደ በቀቀን የሚቀረውበት ቦታም አይደለም። ትምህርት ቤት ልጆች ማጥናትን የሚማሩበት፣ ከእውነታ ጋር ለመጋፈጥ የሚዘጋጁበት፣ እንዲሁም ይህንን እውነታ በብቃት መወጣት የሚማሩበት ብሎም የዛሬዎቹ አዋቂዎች ወደ ኋለኛ፣ መካከለኛ ወይም ወደ እርጅና ዘመናቸው ሲገቡ የሚኖረውን የነገውን ዓለም ለመረከብ የሚዘጋጁበት ቦታ ነው።

ህሊናው የደነዘዘ ወንጀለኛ መማርን አልተማረም። ፍርድ ቤቶች ይህ ወንጀለኛ በድጋሚ ወንጀል ፈፅሞ ቢገኝ እንደገና ወደ ማረሚያ ቤት እንደሚገባ ደጋግመው ሊያስተምሩት ይሞክራሉ። ብዙዎቹ ግን ያንኑ ወንጀል በድጋሚ ይፈጽሙና ተመልሰው እስር ቤት ይገባሉ። እውነታው ሲታይ ብዙ ህግጋት እንዲወጡ ምክንያት የሚሆኑት ወንጀለኞች ናቸው። ስርዓታማ የሆነው ዜጋ ህግን ይታዘዛል፣ በአጠቃላይ ሲታይ ግን ወንጀለኞች ህግን አያከብሩም። ወንጀለኞች ሊማሩ አይችሉም። አንድ ሰው መማርን የማያውቅና መማር የማይችል ከሆነ በዓለም ላይ ያሉ ትእዛዛትና መመሪያዎች ብሎም ቅጣቶች በአንድ ላይ ቢሰበሰቡ እንኳን አይለውጡትም።

አልፎ አልፎ በታሪክ እንደታየው፣ የመንግስት ወንጀለኛ መሆን የመሪዎቹን መማር አለመቻል የሚያሳይ ነው። የታሪክ መዛግብትም ሆኑ ህሊናቸው የሚነግራቸው ጭቆና አደጋን እንደሚያስከትል ነው። ይሁንና እነርሱን ለማስወገድ ግን ከፍተኛ አብዮት ማካሄድ አስፈልጓል። ወይም ሂትለርን ለማስወገድ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተቀስቅሷል። እነዚህ ደግሞ በሰው ዘር ታሪክ ውስጥ ጠባሳ ጥለው ያለፉ ክስተቶች ናቸው። እነዚህ ሰዎች አልተማሩም። በተሳሳቱ መረጃዎች ይፈነጥዛሉ። እውነትንና ማስረጃዎችን ሁሉ ለመቀበል ፈቃደኞች አልሆኑም። መወገድ ነበረባቸው።

አእምሮአቸው የዞረባቸዉ ሰዎች ሊማሩ አይችሉም። ስውር በሆኑ ክፋ ሃሳቦች ስለሚነዱ ወይም ለመገመት የሚያስቸግር ጉዳት ስለደረሰባቸው እውነታንና እውነትን መቀበል ይከብዳቸዋል። የተሳሳቱ መረጃዎችን ህያው አድርገው ያቀርባሉ። ማስተዋል ወይም መማር ፈፅሞ አይችሉም።

መማር ካለመቻል ወይም ለመማር ፈቃደኛ ካለመሆን የሚመጡት የግልና ማህበራዊ ችግሮች እጅግ በርካታ ናቸው።

በዙሪያህ ያሉት አንዳንድ ሰዎች ህይወት ከመስመር ወጥቷል። ምክንያቱም ስላልተማሩ እንዴት ማጥናት እንዳለባቸዉ አያውቁም። ምክንያቱም አልተማሩም። አንተ ራስህ የምታውቃቸው ምሳሌ የሚሆኑ አንዳንድ ሰዎች ይኖሩ ይሆናል።

አንድ ሰው በዙሪያው ያሉ ሰዎች እንዲያጠኑና እንዲማሩ ማድረግ ካልቻለ የራሱ ስራ እንኳን ሳይቀር ከባድ ሊሆንበትና የሥራ ጫና ሊበዛበት ብሎም በህልውና የመቆየት አጋጣሚው ራሱ በእጅጉ ሊቀንስበት ይችላል።

አንድ ሰው ሌሎች እንዲያጠኑና እንዲማሩ መርዳት የሚችለው ሊያገኙ የሚችሉትን መረጃ እንዲያገኙ ካደረገ ብቻ ነው። ለተማሩት ነገር በማበረታታት እውቅና በመስጠት ብቻም መርዳት ይቻላል። ብቃታቸውን ሲያሳድጉ አድናቆትን በመግለጽ ብቻም መርዳት ይቻላል። አንድ ሰው ከፈለገ ከዚህም የበለጠ ማድረግ ይችላል። ለምሳሌ፣ ያለ ክርክር የተሳሳቱ መረጃዎችን እንዲለዩ በማድረግ፣ ያልተረዷቸውን ቃላት እንዲለዩ በመርዳትና ግልጽ በማድረግ እንዲሁም ማጥናትና መማር የማይፈልጉበትን ምክንያት በድጋሚ እንዲያጤኑና ከዚያም ለመማርና ለማጥናት እንዲነሳሱ በማገዝ መርዳት ይቻላል።

ህይወት በአብዛኛው በሙከራና በመሳሳት ላይ የተሞላ ስለሆነ ስህተት የሰራውን ሰው ከመኮነን ይልቅ ስህተቱ እንዴት ሊፈጠር እንደቻለና ሌሎች ከዚህ ስህተት የሚማሩት ነገር መኖር አለመኖሩን ለማስተዋል ሞክር።

አንድ ሰው እንዲማርና እንዲያጠና በማድረግ ብቻ ህይወቱን ማስተካከል መቻልህን ስትመለከት ትገረማለህ። ይህን ማድረግ የሚቻልባቸው ብዙ መንገዶች እንደምታውቅ እርግጠኛ ነኝ። አንዳንዶቹ በጣም የተሻለ ለውጥ ስያመጡ ታያለህ ብዬ አስባለሁ። ዓለም መማር በማይችሉ ሰዎች ጫንቃ ላይ የሚያሳርፈው ሸክም ራሱ ከባድ ነው።

17-3. ት ለማመድ።

ትምህርት ፍሬ የሚያፈራው ተግባር ላይ ሲውል ነው። እርግጥ ጥበብን ለማግኘት ሲባል ብቻ ጥበብን መከታተል ይቻላል፣ ጥበብ የራሱ የሆነ ውበትም አለው። ሆኖም እውነቱን ለመናገር አንድ ሰው ያገኘውን እውቀት በስራ ላይ አውሎ ውጤቱን እስኪያየው ድረስ ጥበበኛ መሆኑን በእርግጠኝነት ማወቅ አይችልም።

ጉድጓድ መቆፈርም ይሁን ህግ፣ ምህንድስና፣ ምግብ ማብሰል ይሁን ሌላ ማንኛውም ተግባር፣ ክህሎት ወይም ሙያ የቱንም ያህል የተጠናም ቢሆን መጨረሻ ላይ አፍጥጠ የሚጠብቀው ጥያቄ ግለሰቡ ይህንን ያገኘውን እውቀት *ሰራ ላይ ሊያውለው* ይችላል ወይ? የሚለው ይሆናል። ይህ ደግሞ *መለማመድን* ይጠይቃል።

ድንቅ ትርዒት የሚያሳዩ የፊልም ሰዎች መጀመሪያ ላይ በቂ ልምምድ ካላደረጉ ጉዳት ሊደርስባቸው ይችላል። የቤት አመቤቶችም ሁኔታ ቢሆን ከዚህ የተለየ አይደለም።

ብዙውን ጊዜ ለደህንነት ሲባል የሚደረገውን ጥንቃቄ የሚዳስስ ርዕሰ ጉዳይ በብዙዎች ዘንድ አትኩሮት አያገኝም። ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ ከዚህ *ጋር* ተያይዘው የሚነሱት "ተጠንቀቅ" እና "ቀስ በል" የሚሉት ነገሮች ስለሆኑ ሰዎች ገደብ እንደተጣለባቸው ሆኖ ይሰማቸዋል። ሆኖም አንድ ሰው በክህሎቱም ሆነ በቅልጥፍናው ረገድ በቂ ልምምድ ካለው "መጠንቀቅ" ወይም "ቀስ ማለት" አያስፈልገው ይሆናል። አንድን

ነገር ችግር ሳያስከትሉ በፍጥነት ማከናወን የሚቻለው የዳበረ ልምምድ ሲኖር ነው።

አንድ ሰው ያለው ክህሎትና ቅልጥፍና ከሚኖርበት ዘመን ፍጥነት ጋር የሚጣጣም መሆን ይኖርበታል። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ በልምምድ ነው።

አንድ ሰው የአካል ክፍሎቹ እርስ በርስ "ተናብበው" መስራት እስኪችሉ ድረስ ሰውነቱን፣ ዓይኑን፣ እጁንና እግሩን በልምምድ ማሰልጠን ይችላል። አንድ ሰው ምድጃውን ለመለኮስ ወይም መኪናውን ለማቆም "ማሰብ" አያስፈልገውም። በደመ ነፍስ *ያደርገዋል*። ማንኛውም እንቅስቃሴ ወደ "ተሰጥዎነት" የሚሸጋገረው *በልምምድ* ነው።

አንድ ሰው ስለ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ማሰብ ሳያስፈልገው አንድን ነገር ሊሰራ ብሎም እየደጋገመው በሄደ መጠን ስለ ጉዳዩ ጭራሽ ሳያስብ በፍጥነትና በትክክል ሊሰራው ይችላል። ይህንን ካላደረገ ግን አደጋ ሊያጋጥመው ይችላል።

አሃዛዊ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ብዙ ልምምድ በሌለበት ብዙ አደጋዎች ያጋጥማሉ።

ይኸው መሰረታዊ ስርዓት በዋነኝነት አእምሮን ብቻ ለሚጠይቁ ሙያዎችም ይሠራል። የፍርድ ቤት ስነ ሥርዓቶችን ደግሞ ደጋግሞ በመለማመድ በጭንቅላቱ ለመቅረጽ ጥረት ያላደረገ ጠበቃ እንደሚቀያየሩት የፍርድ ጉዳዮች ሁኔታ ቶሎ አስተሳሰቡን ማስተካከል ስለማይችል ተሸናፊ ይሆናል። ሥራውን በደንብ ያላጠና አንድ የአክሰዮን ደላላም በደቂቃዎች ውስጥ ከፍተኛ ዕድል ሊያመልጠው ይችላል። የሽያጭ ሥራውን በሚገባ ያልተለማመደ የሽያጭ ሠራተኛም ላይሳካለት ይችላል። ለዚሁ ሁሉ መፍትሔው መለማመድ መለማመድ መለማመድ ነው!

አንዳንድ ጊዜ አንድ ሰው የተማረውን ነገር በስራ ላይ ማዋል እንደማይችል ይገነዘባል። እንደዚያ ከሆነ ችግሩ ያለው የአጠናን ዘይው ላይ ወይም አስተማሪው ወይም መማሪያ ፅሁፉ ላይ ነው። አንድን መመሪያ ማንበብ አንድ ነገር ሆኖ ይህንን

ስራ ላይ ማዋል ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ፍፁም የተለየ ነገር ይሆናል።

አሁንም አሁንም አንድ ሰው በልምምዱ ምንም የተሻለ ነገር ማከናወን ካልቻለ መጽሀፉን ወርውሮ እንደገና እንደ አዲስ መጀመር ይኖርበታል። የፊልም ድምጽ ቀረፃ ሥራ ሁኔታ ከዚሁ ጋር ይመሳሰላል። የቅጂ መብሕፍቱን መመሪያ ተከትለህ የወፍ ድምጽ ለማምጣት ብትጥር የታፈነ ድምጽ ከማሰማት ያለፈ ነገር ማከናወን አትችልም። በአንዳንድ ፊልሞች ላይ የሰዎቹ ንግግር ጥርት ብሎ የማይሰማው ለዚህ ነው። አንድ ጥሩ የድምጽ ቅጂ ሠራተኛ ጥሩ ሥራ ለማውጣት ሁሉን ነገር ትቶ በራሱ መንገድ ማከናወን ነበረበት። ሆኖም በዚህ የሲኒማ መስክም ራሱ በተቃራኒው ጥሩ ነገር ይንጸባረቃል። የሲኒማ ብርሃን ጽሑፎች በጣም ድንቅ ናቸው። እነርሱን ተከትሎ በትክክል የሚሠራ ሰው ጥራት ያለው ምስል ማውጣት ይችላል።

በተለይ በጣም ከፍተኛ ፍጥነት ያላቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶች ባሉበት ህብረተሰብ ውስጥ ሁሉንም ተግባራት በበቂ ሁኔታ ለመረዳት በሚያስችል መንገድ ግልፅ በሆነ ጽሁፍ አለመብራራታቸው በጣም ያሳዝናል። ሆኖም ይህ ሊገታህ አይገባም። ጥሩ ጽሁፎች ሲኖሩ ከፍ ያለ ዋጋ በመስጠት በሚገባ አጥናቸው። ይህ በማይኖርበት ጊዜ ያለውን መረጃ አሰባስበህ በማጥናት የቀረውን ራስህ ለመሙላት ሞክር።

ሆኖም ንድፈ ሃሳብና መረጃ የሚጎለብተው በተደጋጋሚ ተግባር ላይ ሲውል ብቻ ነው።

በዙሪያችን ያሉ ሰዎች አንድን ነገር በደንብ መተግበር አስኪችሉ ድረስ የማይለማመዱ ከሆነ አደጋ ተጋርጠብናል። በ"በቂ ችሎታ" እና በሙያዊ ክህሎት እንዲሁም በቅልጥፍና መካከል ሰፊ ልዩነት አለ። ይህንን ልዩነት የሚደፍነው ደግሞ ልምምድ ነው።

ሰዎች እንዲያስተውሉ፣ እንዲያጠኑ፣ እንዴት ሊሰሩበት እንደሚችሉ እንዲያስቡና፣ ከዚያም እንዲሰሩ አድርግ። ልክ

አንደ ባለሙያ ጥርት አድርገው በትክክል መስራት አስኪችሉ ድረስ ደግመው ደጋግመው አንዲለማመዱት አድርግ።

ክህሎት፣ ቅልጥፍናና ነገሮችን በፍጥነት የማከናወን ችሎታ የሚያስገኘው ደስታ የላቀ ነው። ያለ ችግር ሊከናወን የሚችለው ልምምድ ሲኖር ብቻ ነው። በጣም ፈጣን በሆነ አለም ውስጥ ዝግተኛ ከሆኑ ሰዎች ጋር መኖር አስተማማኝ አይደለም።

ወደ ደስታ በሚመራው ጎዳና ላይ በተሻለ መንገድ መጓዝ የሚቻለው ብቁ ከሆኑ አጋሮች ጋር ነው።

18. የሌሎችን ሃይማኖታዊ እምነት አክብር

መቻቻል የሰዎችን ግንኙነት ለመገንባት ወሳኝ የማዕዘን ድንጋይ ነው።

ሃይማኖታዊ መቻቻል በመጥፋቱ ምክንያት በታሪክ ዘመናት የተሰውትን ሰዎችና የደረሰውን መከራ ስናስብ አለመቻቻል ጸረ ህልውና ተግባር መሆኑን መገንዘብ እንችላለን።

ሃይማኖታዊ መቻቻል ማለት አንድ ሰው እምነቱን መግለጽ አይችልም ማለት አይደለም። ከዚህ ይልቅ የሌላውን ሰው ሃይማኖታዊ እምነት ማጣጣል ወይም መንቀፍ ለችግር የሚዳርግ አቋራጭ ነው ማለት ነው።

ከጥንቱ የግሪክ ዘመን አንስቶ ፈላስፎች አምላክን፣ የሰውን ልጅና የዕንፈ ዓለምን ምንነት በተመለከተ እርስ በርሳቸው ሲከራከሩ ኖረዋል። ከላይ ያሉት ሰዎች ሐሳብ ይንሸራሸራል። ጥንታዊነታቸው የግብጽንና የግሪክን ዘመን ያህል የቆየው የሜካኒካዊና[37] ቁስ አካላዊ[38] አስተሳሰቦች ዛሬ እንደ ፋሽን እንደመግነናቸው ሁሉም ነገር ቁስ አካል ብቻ ነው ብለው ይከራከራሉ። የአዝጋሚ ለውጥ ማብራሪያቸው የቱንም ያህል እንከን የለሽ ሊሆን ቢችልም ያልተገነዘቡአቸው ነገሮች ሊኖሩ

37. ሜካኒካዊ፦ ሕይወት ማለት የቁስ አካል አንቅስቃሴ ሲሆን በፊዚካዊ ሕጎች ትንቃኔ ሙሉ በሙሉ ሊብራራ ይችላል የሚል አምነት ነው። የፍልስፍናው አራማጆች ሉኪፐስና ዲሞክሪቶስ (460 ዓአ አስከ 370 ዓአ) ሲሆኑ ይህንን ፍልስፍና ያገኙት ከግብጻውያን አፈ ታሪክ ሳይሆን አይቀርም። የዚህ ፍልስፍና አቀንቃኞች ሃይማኖትን በስሌት ማስረዳት ስለማይቻል ሃይማኖት አንደማያስፈልግ ተሰምቷቸዋል። ከሃይማኖታውያን ጥቃት የደረሰባቸው ሲሆን አነርሱም በተራቸው ሃይማኖትን አጥቅተዋል። የቦይሌን የፊዚክስ ሕግ ያገኘው ሮበርት ቦይሌ (1627 አስከ 1691) ተፈጥሮ በአንቅስቃሴ ላይ ያለን ቁስ አካል የመሳሰሉ ንድፎች ሊኖሩት ይችሉ ይሆናል የሚል ጥያቄ በማንሳት ፍልስፍናውን ውድቅ አድርጎታል።

38. ቁስ አካላዊ፦ አጽናፈ ዓለሙ ትንሽም ይሁን ትልቅ አንደ ድንጋይ ያሉትን ጠጣር ነገሮች የያዘ ነው ከሚለው የሜታፊዚካዊ ፍልስፍና ዝርያዎች መካከል አንዱን ያመለክታል። ቁስ አካላዊነት ጥንታዊ ንድፈ ሐሳብ ሲሆን ሌሎችም አሉ።

የሚችሉ የመሆኑን ተጨማሪ ሐቅ ችላ ይላሉ። እነዚህ በዛሬው ጊዜ “ኦፊሴላዊ” ፍልስፍናዎች የተደረጉ ሲሆን በትምህርት ቤቶች እንኳ ሳይቀር በትምህርት መልክ ይሰጣሉ። እነዚህ የሌሎችን እምነትና ሃይማኖታዊ አቋም የሚያጣጥሉ የራሳቸው ቀናዒ ተከታዮች አሏቸው። የዚህም ውጤት አለመቻቻል እና ጠብ ሊሆን ይችላል።

ከአምስተኛው መቶ ዘመን ክክርስቶስ ልደት በፊት ወይም ከዚያም በፊት ካለው ዘመን አንስቶ ያሉት ብልህ ሰዎች ሃይማኖታዊ ወይም ፀረ ሃይማኖት አስተሳሰብን በተመለከተ ስምምነት ላይ መድረስ ባይችሉ ኖሮ ሰው ሁሉ የሚሸሸው የጠርነት መድረክ ይሆን ነበር።

በዚህ የቅራኔ ባህር ውስጥ አንድ ብሩህ መሰረታዊ መመሪያ ብቅ ብሏል። እያንዳንዱ ሰው የመረጠውን የማመን መብት አለው “እምነት” የግድ በሎጂክ ሊተነተን አይችልም። ሎጂክን ያልተከተለ ነው ሊባልም አይችልም። እምነት ከዝያ በላይ የሆነ ነገር ነዉ።

አንድ ሰው ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ለሌላ ሰው የሚሰጠው ምክር ይበልጥ ጥሩ የሚሆነው እያንዳንዱ ሰው የመረጠውን የማመን መብት አለው የሚለውን አመለካከት የሚያንጸባርቅ ከሆነ ነው። አንድ ሰው የራሱን እምነት የመያዝ መብት አለው። አንድ ሰው የሌሎችን እምነት ለመዝለፍ ይበልጡንም ደግሞ ሌሎችን በሃይማኖታዊ አቋማቸው ምክንያት ለማጥቃት ወይም ለመጉዳት ይሞክር እንደሆነ ችግር ውስጥ ይገባል።

የተለያዩ ዝርያዎች ብቅ ካሉበት ጊዜ አንስቶ የሰው ልጅ በሃይማኖቱ በአጅጉ ሲጸናና እንዲሁም ሲደሰት ኖሯል። የዛሬዎቹ “የሜካኒካዊ” እና “ቁስ-አካላዊ” አማኞች እንኳ የራሳቸውን ቀኖና እንደሚያሰራጩት እንደ ጥንቶቹ ካህናት ሆነዋል።

እምነት የሌላቸው ሰዎች የሚታዘንላቸዉ ናቸዉ። የሚያምኑበት ነገር ሊሰጣቸው ይችላል። ሆኖም ሃይማኖታዊ እምነት ካላቸው ይህንን እምነታቸውን አክብርላቸው።

አንድ ሰው የሌላውን ሰው ሃይማኖታዊ እምነት ማክበር ካቃተው ወደ ደስታ የሚመራው ጎዳና ጠብ የበዛበት ሊሆን ይችላል።



19. በራስህ ሊደረግብህ የማትፈልገውን በሌሎች ላይ ላለማድረግ ሞክር።

በብዙ አገሮች በሚኖሩ ብዙ ሰዎች ዘንድ ለብዙ ዘመናት "ወርቃማው ህግ"[39] በመባል የሚታወቅ አንድ አባባል አለ። ከላይ ያለው የጥቅሱ አቀማመጥ ጎጂ የሆኑ ተግባራትን የሚመለከት ነው።

አንድም ቀን ሌሎችን ሳይጎዳ መኖር የሚችለው ቅዱስ ብቻ ነው። ሆኖም ሳያመዛዝን በዙሪያው ያሉትን ሰዎች የሚጎዳው ወንጀለኛ ብቻ ነው።

ከ "ጥፋተኝነት" ወይም "ከሐፍረት" ወይም "ከህሊና ወቀሳ" በተጨማሪ አንድ ሰው በሌሎች ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ዞሮ ዞሮ ለራሱም ይተርፈዋል።

ውጤታቸው ሊቀለበስ የሚችለው ሁሉም ጉዳቶች አይደሉም። አንድ ሰው ሊታለፍ ወይም ሊረሳ የማይቻል ጥፋት ሊፈጽም ይችላል። ነፍስ ግድያ አንዱ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ማናቸውንም ሃሳቦች በጉልህ መጣስም ቢሆን በሌላው ላይ ሊቀለበስ የማይችል ጎጂ ድርጊት መፈጸም ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ይቻላል።

የሌላውን ሰው ህይወት ማጥፋት የራስን ህይወት ማበላሸት ነው። ማህበረሰቡ የሚሰጠው ምላሽ ይኖራል። ማረሚያ ቤቶችና የአእምሮ ጉዳተኛ መሰብሰቢያዎች የተሞሉት መሰሎቻቸውን

---

39. "ወርቃማው ህግ"፦ ምንም እንኳን ይህ በክርስቲያኖች ዘንድ የክርስትና አስተሳሰብ እንደሆነ የሚታሰብ ቢሆንም እንዲሁም በአዲስና በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም በብዙ ዝርያዎችና ሕዝቦች ዘንድ የተለመደ አባባል ነው። ይኸው አባባል በኮንፊሺየስ (በአምስተኛውና በስድስተኛው መቶ ዘመን ዓ.አ) የተጠቀሰ ሲሆን አርስም የጥንት መጻሕፍትን ጠቅሶ የተናገረው ነው። በማም ጥንታዊ በሆኑ ነገዶች ዘንድም የሚታወቅ አባባል ነው። በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በጥንታዊ የፐርሳቶ፣ አርስቶትል፣ ሶቅራጥስ እና ሴኔካ ሥራዎች ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል። ለብዙ ሺህ ዓመታት ሰዎች የመልካም ምግባር መለኪያ አድርገው ሲቆጥሩት ኖረዋል። ይሁን እንጂ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያለው አቀማማጥ ለየት ያለ ነው። ቀደም ባለው አቀማመጡ ቢቀመጥ አንድን ንድፈ ሐሳብ የሚደግፍ ሊመስል ይችላል ተብሎ ታስቧል። ይህንንም አቀማመጥ መጠቀም ይቻላል።

በጎዱ ሰዎች ነው። ሆኖም አንድ ሰው በሌሎች ላይ ጎጂ ድርጊት ከፈፀመ በኋላ ተያዘም አልተያዘ ሌሎች ቅጣቶች ይኖራሉ። በተለይ ጥፋቱ የተፈፀመው በድብቅ ከሆነ አንድ ሰው ስለ ሌሎችም ሆነ ስለ ራሱ ባለው አመለካከት ላይ ሥር የሰደደ ተጽዕኖ ሊያሳድርበት ይችላል። የህይወት ደስታና ጣእም ይጠፋበታል።

ይህ "የወርቃማው ህግ" ትርጓሜ እንደ መፈተኛም ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። አንድ ሰው ሌላውን ሰው ይህንን ህግ ተግባራዊ እንዲያደርግ ካሳመነው ጎጂ ተግባር *ምን እንደሆነ* እውነታውን እንዲገነዘብ ረዳው ማለት ነው። *ጎጂ ተግባር* የሚባለው ምን እንደሆነ ለዚያ ሰው ግልጽ ይሆንለታል። *ስህተት* መፈፀምን በተመለከተ የሚነሳው የፍልስፍና ጥያቄ ማለትም ስህተት መፈፀም ምንድን ነው የሚለው ክርክር በግለሰብ ደረጃ ወዲያው መልስ ያገኛል። ይህ በራስህ ላይ እንዲደርስ ትፈልጋለህ? አትፈልግም? *ታዲያ* በአንተ ላይ እንዲደርስ ካልፈለግህ ጎጂ ተግባር ከመሆኑም ሌላ ከማህበረሰቡ አይታ አንፃር ስህተት ነው ማለት ነው። ይህ የህብረተሰቡ ዓይን እንዲገለጥ ያደርጋል። ከዚያም አንድ ሰው ምን ማድረግ አለበት ምንስ ማድረግ የለበትም የሚለውን ግልፅ ያደርጋል።

አንድ ሰው ጎጂ ተግባራትን ለመፈጸም ምንም ገደብ እንደሌለበት በሚሰማው ጊዜ በህልውና የመቆየት አቅሙ በእጅጉ ይመነምናል።

ሰዎች ይህንን ተግባራዊ እንዲያደርጉት ማሳመን ከቻልክ የራሳቸውን ህይወት መመርመር የሚችሉበትንና ለአንዳንዶችም እንደገና ከሰው ዘር *ጋር* የሚቀላቀሉበትን በር የሚከፍት ቁም ነገር አስጨበጥካቸው ማለት ነው።

ወደ ደስታ የሚመራው ጎዳና በሌሎች ላይ ጎጂ ተግባራት ከመፈፀም ለማይቆጠቡ ሰዎች ዝግ ነው።

20. ሌሎች አንተን እንዲይዙህ በምትፈልግበት መንገድ ሌሎችን ለመያዝ ሞክር።

ይህ “የወርቃማው ህግ” አዎንታዊ ገጽታ ነው።

አንድ ሰው “ቀና ሰው እንዲሆን” ስትነግረው ቅሬታ ቢሰማው አትገረም። ቅሬታ የሚሰማው “ቀና በመሆን” ጉዳይ ላይ ሳይሆን ግለሰቡ ይህ ምን ማለት እንደሆነ በትክክል ባለመረዳቱ ሊሆን ይችላል።

አንድ ሰው “መልካም ባህርይ” ማለት ምን ማለት ሊሆን እንደሚችል እርስበርስ የሚቃረን እና የተምታታ ሀሳብ ውስጥ ሊገባ ይችላል። አንድ ሰው በትምህርት ቤት ለ”ጠባይ” ነጥብ የተሰጠው ለምን እንደሆነ መምህሩ ሊያውቅ እንኳ ቢችልም እርሱ ግን ላይገነዘበው ይችላል። ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተም የተሳሳተ መረጃ ደርሶት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ያህል፣ “ልጆችን ማየት እንጂ ማዳመጥ አያስፈልግም” ወይም “ጥሩ መሆን ማለት ዝም ማለት ነው” የሚሉትን ዓይነት የመሳሰሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

ሆኖም ይህንን ጉዳይ አንድን ሰው ሙሉ በሙሉ ሊያረካ በሚችል መንገድ ግልጽ ማድረግ የሚቻልበት ዘዴ አለ።

በማንኛውም ጊዜና በብዙ ቦታዎች የሰው ልጅ ከፍተኛ ግምት የሰጣቸው እሴቶች አሉ። እነዚህ *ቦንነት*[40] ተብለው ይታወቃሉ። እነዚህ እሴቶች የመነጩት ከጥበበኛ ሰዎች፣ ከቅዱሳንና ከአማልክት ነው ተብሎ የሚታመን ሲሆን ባልሰለጠኑና በሰለጠኑ ሰዎች መካከል እንዲሁም በሁከት በሚታመስና በተረጋጋ ህብረተሰብ መካከል ልዩነት አምጥተዋል።

“ጥሩ” የሚባለው ምን እንደሆነ ለመለየት ከሰማይ ፈቃድ ማግኘትም ሆነ የፈላስፎችን ግዙፍ ዶሴ ማገላበጥ ፈጽሞ አይጠይቅም። በጉዳዩ ላይ የግል መረዳት ብቻውን በቂ ነው።

40. በጎነት፦ መልካም ሰብዓዊ ባሕርያት።

በማንኛውም ሰው ለማለት ይቻላል ሊሰራ የሚችል ነገር ነው።

አንድ ሰው በሌሎች ምን ዓይነት አያያዝ እንዲደረግለት እንደሚፈልግ ቆም ብሎ ካሰበ ሰብዓዊ የበጎነት ባህርይን ማዳበር ይችላል። ሰዎች እንዴት እንዲይዙህ *እንደምትፈልግ* ብቻ አስብ።

ከሁሉ በላይ *በፍትሃዊ* መንገድ መያዝ እንደምትፈልግ አያጠራጥርም። ሰዎች ስለ አንተ ውሸት እንዲናገሩ ብሎም በሃሰት ወይም አላግባብ እንዲያወግዙህ አትፈልግም። አይደለም እንዴ?

ወዳጆችህና ጓደኞችህ ለአንተ *ታማኝ* እንዲሆኑ ትፈልጋለህ። አሳልፈው እንዲሰጡህ አትፈልግም።

በአእምሮአቸው እንድትያዝ እንጂ እንድትታለል አትፈልግም።

ሰዎች ከአንተ *ጋር* ባላቸው ግንኙነት *ሚዛናዊ* እንዲሆኑ ትፈልጋለህ።

ሐቀኞች እንዲሆኑልህ እንጂ እንዲያጭበረብሩህ አትፈልግም። እውነት አይደለም?

ሰዎች በጭካኔ ሳይሆን *በደግነት* እንዲይዙህ ትፈልጋለህ።

ሰዎች መብትህንና ስሜትህን *ከግምት እንዲያስገቡልህ* መፈለግህ አይቀርም።

በምትተኛዝበት ጊዜ *በርህራሄ* እንዲይዙህ ትፈልጋለህ።

ሌሎች ከሚጮኹብህ *ራሳቸውን ገዝተው* እንዲያነጋግሩህ ትፈልጋለህ። አይደለም?

አንድ አይነት ጉድለት ካለብህ ወይም ስህተት ከፈፀምክ ሰዎች በትዕግስት እንዲይዙህና ነቃፊ እንዳይሆኑብህ ትፈልጋለህ።

ሰዎች ስለ ቅጣት ከሚያስቡ ይልቅ *ይቅር ባይ* ቢሆኑልህ ደስ ይልሃል። አይደለም?

ሰዎች ጨካኝና ቀንቋና ሳይሆን *ደግ* እንዲሆኑልህ ትፈልጋለህ።

ሰዎች በሁሉም ነገር እንዲጠራጠሩህ ሳይሆን *እንዲያምኑህ* ትፈልጋለህ።

መሰደብን ሳይሆን *መክበርን* እንደምትፈልግ የታወቀ ነው።

ሌሎች ሰዎች ትሁት እንዲሆኑልህና ሰብዓዊ ክብርህን አንዲጠብቁልህ ትፈልጋለህ። እውነት አይደለም?

ሰዎች ቢያደንቁህ ደስ ይልህ ይሆናል።

አንድ ነገር ስታደርግላቸው አንዲያመሰግኑህ ትፈልጋለህ። እውነት አይይለም?

ሌሎች ሰዎች ወንድማዊ አቀራረብ አንዲያደርጉልህ ትፈልጋለህ።

ከአንዳንዶችም ፍቅርን ትፈልጋለህ።

ከሁሉም በላይ ደግሞ እነዚህን ባህርያት ለይምሰል አንዲያሳዩህ አትፈልግም። ከዚህ ይልቅ ከውስጥ የመነጨ እውነተኛ ስሜታቸው አንዲሆንና ይህንንም በታማኝነት አንዲያደርጉት ትፈልጋለህ።

ሌሎች ባህርያትንም ማሰብ ትችል ይሆናል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትም ሐሳቦች አሉ። በጎነት ተብለው የተገለፁትንም ጠቅለል አድርገህ ማሰብ ትችል ይሆናል።

አንድ ሰው ሌሎች ሰዎች ዘወትር እርሱን በዚህ መንገድ ቢይዙት ህይወቱ ምን ያህል በደስታ ይሞላ እንደነበር ለመገንዘብ ብዙ ማሰብ አይጠበቅበትም። ደግሞም አንድ ሰው በዚህ መንገድ ለሚይዙት ሰዎች ጥላቻ ያዳብራል ብሎ ማሰብ አዳጋች ነው።

በሰዎች ግንኙነት በጣም አስገራሚ የሆነ ክስተት[41] አለ። አንድ ሰው በሌላው ሰው ላይ ሲጨኽበት ሌላኛው ሰው መልሶ ለመጨኽ ይገፋፋል። አንድ ሰው የሚገጥመው ምላሽ እርሱ ለሌሎች የሚያሳየው አያያዝ ነፀብራቅ ነው። አንድ ሰው፣ ሰዎች እርሱን ለሚይዙበት መንገድ ምሳሌ የሚሆነው ራሱ ነው። "ሀ" ከ"ለ" ጋር ባለው ግንኙነት ጨካኝ ከሆነ "ለ"ም ጨካኝ ይሆንበታል። "ሀ" ከ"ለ" ጋር ባለው ግንኙነት ወዳጃዊ ከሆነ "ለ"ም ወዳጃዊ ይሆንለታል። ይህ ነገር ተግባራዊ ሲሆን እንዳየህ አርግጠኛ ነኽ። ጆርጅ ሴት የተባለውን ሁሉ ይጠላ እንደሆነ ሴቶች ጆርጅን ይጠሉታል። ካርሎስ ሰዎችን ሁሉ በቀና መንገድ

41. ክስተት፦ የሚታይ እውነታ ወይም ክንውን።

የማይዝ ከሆነ ሰዎችም እርሱን በቀና መንገድ አይዙትም። ደግሞ በይፋ አያውጡት እንጂ ለካርሎስ ያላቸው ቀና ያልሆነ አመለካከት አጋጣሚውን ካገኙ እርሱን ለመጉዳት እንዲዘጋጁ ሊያደርጋቸው ይችላል።

የፈጠራ በሆነው በልብ ወለዱና በፊልሙ ዓለም አስገራሚ ብቃት ያለው ተዋናይ የወሮበሎች ቡድን አለቃ ሆኖ ሳለ ትሁት ስለሆነ አመፀኛ እንዲሁም ብቸኛ ስለሆነ አጉራ ዘለል[42] ጀግና ማየት የተለመደ ነው። የሕይወት እውነታ ግን እንደዚያ አይደለም። ዓመጸኛ የሆኑ ሰዎች አስቸጋሪ ባህርይ ያላቸው ሲሆኑ ጭፍራቸው ደግሞ ከእነርሱ የከፋ ነው። ናፖሊዮንንና ሂትለርን አሳልፎ የሰጣቸው የገዛ ህዝባቸው ነው። እውነተኛ ጀግኖች በጣም ረጋ ያሉና ለወዳጆቻቸው ትሁት የሆኑ ሰዎች ናቸው።

በሙያቸው አንቱ የተባሉ ወንዶችና ሴቶችን አግኝቶ የማነጋገር አጋጣሚ ያገኘ ሰው ባላቸው በጣም ጥሩ የሆነ ባህርይ ይማረካል። ደግሞም ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ሊደርሱ የቻሉት በዚሁ ምክንያት ነው። አብዛኞቹ ሌሎች ሰዎችን በጥሩ መንገድ ለመያዝ ይጥራሉ። በዙሪያቸው ያሉትም ሰዎች በምላሹ በበጎ መንገድ ይይዟቸዋል። እንዲሁም ትናንሽ ስህተቶቻቸውን እንኳን ሳይቀር በይቅርታ ያልፉላቸዋል።

አንድ ሰው እርሱ ምን ዓይነት አያያዝ ቢደረግለት ደስ እንደሚለው በመለየት ብቻ በጎ የስነ ምግባር አሴቶች ምን እንደሆኑ ለይቶ ማወቅ ይችላል። በዚህም "ጥሩ ጠባይ" ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ መልስ ያገኛል ቢባል የምትስማማ ይመስለኛል። ይህም ምንም ሳያደርጉ እና ዝም ብሎ በመቀመጥ "ጥሩ ከመሆን" ፈፅሞ የተለየ ሲሆን "ጥሩ መሆን" በድርጊት የሚገለፅና በጠንካራ ተግባራት የሚንጸባረቅ ባህርይ ነው።

ጭጋግ በዋጠው ክብር ተኮፍሶ በመቀመጥ ብቻ የሚገኝ ደስታ አይኖርም። አንዳንድ የጥንት ሰዎች በጎ ምግባር መፈፀምን ህይወትን ማጎሳቆል እንደሆነ አስመስለው ያቀርቡት ስለነበር ደስታ የሚገኘው ክፉ በመሆን ነው ያሉ ያህል ነበር።

---

42. አጉራ ዘለል፦ አለቸጋሪ ባህርይ ወይም ያልታረመ ጠባይ ያለው ሰው።

ደስታ እና ሀሴት ኢ-ሞራላዊ ምግባር በመፈፀም ሉይገኙም/ አንዲያውም እውነታው ተቃራኒው ነው! ደስታ እና ሀሴት የሚገኘው ቀና ከሆነ ልብ ብቻ ነው። ኢ-ሞራላዊ ምግባር የሚፈጽም ሰው ህይወት ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ በህዘንና በስቃይ የተሞላ ነው። ሰብዓዊ የበጎነት ባህርይ ህይወትን የሚያጨልም ሳይሆን ብሩህ ገጽታ የሚያላብስ ነው።

አንግዲያው አንድ ሰው በዙሪያው ያሉትን ሰዎች *በፍትህ፣ በታማኝነት፣ በጥሩ አክብሮት፣ በሚዛናዊነት፣ በቀናነት፣ በደግነት፣ ሁኔታቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ በርህራሄ፣ ራስን በመግዛት፣ በትዕግስት፣ በይቅር ባይነት፣ በአምነት፣ በአክብሮት፣ በትህትና፣ ሰብዓዊ ክብራቸውን በመጠበቅ፣ በአድናቆት፣ በወዳጅነት፣ በፍቅር ለመያዝና* እነዚህን ሁሉ *በእውነተኛ ሰሜትና በታማኝነት* ለማድረግ ቢጥር ውጤቱ ምን የሚሆን ይመስልሃል?

ጊዜ ሊወስድ ቢችልም ሌሎችም ተመሳሳይ ምላሽ ለመስጠት የሚነሳሱ አይመስልህም?

አንዳንድ ጊዜ በጣም አንደሚያበሳጨው የቤት ሰርሳሪ ሌባ፣ ስራ ረፍዶብህ እያለ በፍጥነት በሚነዳበት መስመር ላይ ቀስ ብሎ አንደሚያሽከረክር ወፈፌ ያሉት ሰዎች መንፈስን ሊያስቱ ቢችሉም አንድ ሰው ይህንን ጥረት በማድረጉ ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት ወደ አዲስ ምዕራፍ ይሸጋገራል። በዚህም አንድ ሰው በህልውና የሚቆይበት ጊዜ ይራዘማል። ህይወቱም ደስታ የተሞላበት ይሆናል።

አንድ ሰው በዙሪያው ባሉት ሰዎች ባህርይ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር *ይችላል*። ይህንን እያደረገ ካልሆነ በቀን ውስጥ አንዱን የበጎነት ባህርይ ብቻ በመምረጥ በእለቱ ውስጥ በዚያ ባህርይ ላይ ለመስራት ቢጥር ቀላል ይሆናል። ቀስ በቀስ ደግሞ ሁሉንም የግል ህብቱ ያደርጋቸዋል ማለት ነው።

አንድ ሰው በግል ከሚገኘው ትሩፋት በተጨማሪ የቱንም ያህል ጥቂት ቢሆን አንድ ሰው በሰዎች ግንኙነት መስክ ለሚከፈተው አዲስ ምዕራፍ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላል።

በኩሬ ውስጥ የምወትወድቅ ትንሽ ጠጠር እስከ መዲያኛው ዳርቻ የሚደርስ የውሃ ንቅናቄ ልትፈጥር ትችላለች።

“ሌሎች እንዲያደርጉልህ የምትፈልገውን እንዲሁ አንተም ለሌሎች ለማድረግ ሞክር” የሚለውን መርህ ሰንከተል መደ ደስታ የሚመራው ጎዳና ይበልጥ ብሩህ ይሆናል።



21. እያደግህና[43] እየጎለበትክ[44] ሂድ።

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች እነሱ ምንም ላያገኙና ላያተርፉ ሌሎችን ወደ ታች መደቆስና ተስፋቸውን እና መልካም ምኞታቸውን ማጨለም ይፈልጋሉ።

ክፉ ሃሳብ ያላቸው ሰዎች በሌላው ላይ በመሳለቅና በሌላ በሌላ መንገዶች ለሌላው ውድቀት ሙከራ ለያደርጉ ይችላሉ።

ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን፣ ራስን ለማሻሻልና ይበልጥ ደስተኛ ለመሆን የሚደረገው ጥረት በሌሎች ዘንድ ላይወደድ ይችላል።

አንዳንድ ጊዜ እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ በቀጥታ ለመፍታት መሞከር ያስፈልጋል። ሆኖም አልፎ አልፎ የማይሳካበት ረዥም አካሄድ ይኖራል።

እንደነዚህ ያሉ ሰዎች አላማቸው ምንድን ነው? የአንድን ሰው እድገት ወደ ኋላ ለመጎተት መሞከር ነው። በሆነ መንገድ ሌላው ሰው ለእነርሱ ደህንነት አደገኛ እንደሆነ ይሰማቸዋል። አንድ ሰው ካደገ ለእነርሱ አደገኛ እንደሆነ ያስባሉ። ስለሆነም በተለያየ መንገድ ችሎታውንና ብቃቱን ለማቆርቆዝ ይፈልጋሉ።

አንዳንድ ክፉ ሃሳብ ያላቸው ሰዎች የሚያወጡትን እቅድ በሚከተለው መንገድ ጠቅለል አድርጎ መግለጽ ይቻላል፤ "ሀ ይበልጥ የተሳካለት ሰው ከሆነ ለእኔ አደገኛ ሊሆን ስለሚችል የእርሱን ስኬት ለመቀነስ የቻልኩትን ሁሉ ማድረግ አለብኝ" ብሎ ያስባል። እነዚህ ሰዎች ከዚህ ቀደም ሀ ለእነርሱ ጠላት ያልነበረ ቢሆንም በዚህ ድርጊታቸው ምክንያት ጠላት ሊሆንባቸው እንደሚችል ፈጽሞ አይገነዘቡም። እንደዚህ ዓይነት ጤናማ አስተሳሰብ የሌላቸው ሰዎች ችግር ውስጥ መግባታቸው ሳይታለም የተፈታ ነው። አንዳንዶች ደግሞ ይህን የሚያደርጉት

---

43. ማደግ፦ ምርታማ መሆን፣ በጎ ተጽዕኖን መጨመር፣ የሚታይ ለውጥ ማድረግ።
44. መጎልበት፦ ኤኮኖሚያዊ ውጤት ላይ መድረስ፣ በሥራ ስኬትን ማግኘት።

በስሜታዊ ጥላቻ ተገፋፍተው ወይም “ያንን ሰው ስለማይወዱት” ብቻ ነው።

ይሁን እንጂ ሙከራውን ፈጽመዋል። የእነዚህ ሰዎች ዋነኛ አላማ ያሰቡትን ሰው እድገት መግታትና ህይወቱን ማስተጓጎል ነው።

እንዲህ አይነቱን ሁኔታ ማስተናገድና እንደነዚህ አይነት ሰዎችን ማሸነፍ የሚቻለው በእርግጥ በማደግና በመጎልበት ነው።

አዎን፣ እንዲህ ዓይነት ሰዎች አንድ ሰው ሲሻሻል ሲያዩ ያማቸዋል። ስለሆነም ሙሉ ሃይላቸውን ተጠቅመው ጥቃት ሊሰነዝሩ ይችላሉ። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ችግሩን ለመፍታት ጣር እንጂ ተስፋ ቆርጠህ ማደግህንና መጎልበትህን እንድታቆም፣ ተስፋ እንዲያስቆርጡህም አትፍቀድ። ምክንያቱም የእነርሱ ጥረት እንዳታደግና እንዳትጎለብት ነዉና።

ይበልጥ እያደግህና እየጎለበትክ ከሄድክ እነዚህ ሰዎች ራሳቸው ስልችቷቸው ሁሉንም ነገር ይተዉታል።

አንድ ሰው በህይወቱ የሚከታተለው ግብ ፋይዳ ያለው ከሆነና በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን መመሪያዎች በመከተል ከፈጸመው እንዲሁም እያደገና እየጎለበተ ከሄደ ድል አድራጊ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም። ደግሞም ይህንን ካኬት የሚያገኘው ከፀጉራቸው አንዷን እንኳ ሳትጎዳ ይሆናል።

እኔ የምመኝልህም ይህንኑ ነው።
እንድታድግና እንድትጎለብት!

መደምደሚያ

ደስታ የሚገኘው ጠቃሚ ተግባራትን ከማከናወን ነው። ይሁንና አንድን ሰው ደስተኛ የሚያደርገው ምን እንደሆነ መናገር የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ነው፦ ግለሰቡ ራሱ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት መርሆች የመንገዱ ጠርዝ ናቸው። እነዚህን መርሆች መጣስ ጠርዝ ላይ እንደወጣ ሞተረኛ መሆን ማለት ነው። ውጤቱ ከሌሎች ጋር ያለንን ግንኙነት ማበላሸት ወይም ህይወትን ማጣት ሊሆን ይችላል።

ከሌሎች ጋር ያለህን ግንኙነትና የህይወትህን ግብ የምታወጣው አንተ ስለሆንክ ጎዳናው ወዴት እንደሚመራ መናገር የምትችለው አንተ ብቻ ነህ።

አንድ ሰው አሁን ጊዜው እንዳለፈበት፣ የቀድሞ ጎዳናው የተመሰቃቀለ እንደሆነና የወደፊቱን ጎዳና ማስተካከል የሚችልበት አጋጣሚ እንደሌለ ሊሰማው ይችላል። ሆኖም አንድ ሰው በጎዳናው ላይ በማንኛውም ጊዜ አዲስ ዕቅድ መንደፍ ይችላል። ይህንኑ ለመከተል ሞክር። ሁሉንም ነገር በአዲስ መንፈስ ሊጀምር የማይችል ሰው አይኖርም።

አንዳንድ ሰዎች በሌሎች ሊዘባበቱና እነርሱን ከመንገድ ለማስወጣት ብሎም ሥነ ምግባር የጎደለው አካሄድ እንዲከተሉ ለማድረግ የተለያዩ ዘዴዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ ብሎ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። በተለያየ መንገድ ኢ-ሞራላዊ ወደሆነ ህይወት ለመምራት ሊጥሩ ይችላሉ። እንዲህ የሚያደርጉ ሰዎች አላማቸው የራሳቸውን ጥቅም ማስጠበቅ ነው። የሚያዳምጣቸው ካገኙ ወደ ሐዘንና ውድቀት ሊመሩ ይችላሉ።

እርግጥ አንድ ሰው የዚህን መጽሐፍ ምክር ስራ ላይ ለማዋልና ሌሎች እንዲጠቀሙበት ለማድረግ ሲጥር የተወሰነ ውጣ ውረድ ሊያጋጥመው ይችላል። ሆኖም ከዚያ ትምህርት ወስዶ ወደፊት መግፋት ይኖርበታል። መንገዱ ወጣ ገባ አይኖረውም ብሎ የሚከራከር ማን ነው? እንደዝያም ሆኖ

ለመጓዝ ያስችላል። ሰዎች ሊወድቁ ቢችሉም እንደገና ተነስተው ጉዞአቸውን መቀጠል አይችሉም ማለት አይደለም።

አንድ ሰው የመንገዱን ጠርዝ ጠብቆ ከተጓዘ የከፋ ስህተት ከመፈፀም ይድናል። እውነተኛ እርካታ፣ ደስታና ሃሴት የሚገኘው ከተመሰቃቀለ ህይወት አይደለም።

ሌሎች በዚህ ጎዳና እንዲሄዱ ማድረግ ከቻልክ አንተ ራስህ እውነተኛ ደስታ ምን ማለት እንደሆነ ለመገንዘብ የሚያስችል አጋጣሚ ታገኛለህ።

ወደ ደስታ የሚመራው ጎዳና የመንገዱን ጠርዝ የሚያውቁ ሰዎች በከፍተኛ ፍጥነት የሚነዱበት መንገድ ነው።

ሹፌሩ አንተ ነህ።

መልካም መንገድ።

© 2005 L. Ron Hubbard Library. የባለቤቱ መብት የተጠበቀ ነው። የኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎችን ጨምሮ በማንኛውም መልኩ በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ያለ ፈቃድ መገልበጥ፣ መቅርጎም፣ ማባዛት፣ ማሰራጨት፣ ማስተመጥ፣ ወይም ማስተላለፍ ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሕጎች መጣስ ይሆናል። THE WAY TO HAPPINESS (“ዘ ዌይ ቱ ሃፒነስ”) እና “Road & Sun” (“ሮድ ኤንድ ሰን”) የሚሉት የንግድ ምልክቶች በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካም ሆነ በሌሎች አገሮች ውስጥ L. Ron Hubbard Library ባለቤትነት የተመዘገቡና (የንግድ ምልክት ምዝገባ ተሰጥቶአቸው ሌሎች ምዝገባዎች በሂደት ላይ ናቸው።) ፈቃድ ሲገኝ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው።

የዚህን መጽሀፍ ተጨማሪ ቅጂ ለማግኘት፣

The Way to Happiness Foundation International
201 E. Broadway, Glendale, CA 91205 USA
800-255-7906 or 818-254-0600
Fax: 818-254-0555
Email: info@twth.org
Website: www.thewaytohappiness.org

ይህ ሙሉ በሙሉ በመሰረታዊ መመሪያዎች ላይ የተመሰረተና የጽሞናዊ ያልሆነ የመጀመሪያው የሰው ምግባር ደንብ ነው። አዘጋጁ ኤል ሮን ሄበርድ ነው። ጽሑፉም የዚህ ግሰሰብ የሥራ ውጤት ሲሆን የየትኛውም ሃይማኖታዊ ቀናና አካል አይደለም። ይህንን ስውሩ ዐድጋጊ ማሳተምም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ግሰራጨት ከማገኛውም ሃይማኖታዊ ድርጅት ጋር ግንኙነት የሌለው ተግባር ይሆናል። በመሆኑም የመንግስት አካላትና ሰራተኞች ስርዓቱን እንደ ሃይማኖታዊ አንትስተሰሲ አለመቁጠራቸው ተገቢ ይሆናል። (ሳንም ሀትመቱ ክፅጀ ሳለመብቱ ወይም ክባለ ወኪሎቹ ጋር በሚደረግ ዝግጅት ሊከናወን ይችላል።)

Amharic Edition